# የትያጥሮን ቤተ ክርስቲያን ዘመን

ዛሬ ማታ... ወደ ታላቁ የቤተ ክርስቲያን ዘመን ከማለፋችን በፊት... ጌታ መንፈሱ በእኛ ላይ እንዲያፈስብን እና... እንዲባርከን ተስፋ— አደርጋለሁ። ለጊዜው ዋና ዋና አሳቦችን ብቻ እንዳሰሳለን፡ በቀጣይ ታላቅ ዝግጅት፡ ሳምንቱን ሙሉ እዚህ እነሆናለን። አቤት፡ ትናንት ማታ፡ እጅግ ድንቅ ጊዜ አሳልፈናል!

2 አሁንም፡ ቅዱስ ቃሉን ከማንበባችን በፊት፡ ከቻልን ለአፍታ ያህል አቅጣጫችንን—ቀይረን ለመጸለይ እንቆማለን።

3 ቸር የሰማይ አባታችን ሆይ፡ ሁሉን-በሚችለው ስም በጌታ በኢየሱስ ቀርበናል፡ አንድ ቀን እንደምትመጣ እናውቃለንና። አንተ ለዘላለም ሕያው ሆነህ የምትኖር የሕያው የእግዚአብሔር ልጅ እንጂ ሙት አለመሆንህን፡ የመታደስ ዘመን ከጌታ መገኘት በሚመጣበት፡ በዚህ ታላቅ ጊዜ፡ የጴንጤቆስጤ ምስክር ሆነህ በገዛ በቤተ ክርስቲያንህ ውስጥ የምትኖር መሆንህን፡ ይህን ታላቅ መገለጥ እንዲቀበሉ የሰዎች ልብ ለማዘጋጀት እየሰራን እንገኛለን። ከአሰራ ዘጠኝ መቶ አመታት በኋላ እነኚያ ወቅቶችን ማጣጣም በመቻላችን እጅግ ሐሴት እናደርጋለን።

4 አሁንም፡ አባት ሆይ፡ በዘመናት ሁሉ በእጅህ ውስጥ የነበሩትን ታላላቅ ሰዎችን፡ አገልጋዮቹን "የቤተ ክርስቲያን ዘመናት መላእክት፡" ናቸው ያልካቸው፡ እነዚያን ከዋክብቶች ለማክበር፡ እራሳችንን ዝቅ እናደርጋለን። ሰለ ኤፌሶኑ ቅዱስ፡ ሰለ ታላቁ ጳውሎስ እጅግ እናመሰግንሃለን። ጌታ ሆይ፡ ሰለ ኢራኔዎስም እጅግ እናመሰግንሃለን፡ ሰለ ታላቁ ባርያህ ኢራኔዎስ፡ እንዲሁም ሰለ ቅዱስ ማርቲን፡ ዛሬም ምሽትም ሰለ ቅዱስ ኩሉምባ። ጌታ ሆይ፡ ሰለነዚህ ሰዎች ሁሉ እናመሰግንሃለን። በቤተ ክርስቲያን ላይ በመጣው፡ ታላቅ የሮማኒዝም፡ እና አረማዊነት ጨለማ ፊት፡ በልሳኖች እየተናገሩ፡ እና ታላላቅ ድንቆች እና ምልክቶችን እያሳዩ፡ በሽተኞችን እየፈወሱና፡ ሙታንን እያስነሡ—ሰለ ጴንጤቆስጤ መልእክትና በረከት በድፍረት ጸኑ።

5 ጌታ ሆይ፡ ብዙዎቻቸው፡ ተሰነጠቁ፡ ተገደሉ፡ ለአንበሶች ተሰጡ፡ ታላላቅ ነገሮች ተፈጽሞባቸዋል። ምድር በጻድቃን ደም ራሰች። አባት ሆይ፡ ሰለ ክፉዋና አመንዝራዋ ቤተ ክርስቲያን፡ ዛሬም፡ ደማቸው ይጮኻል። አንተም አንድ ቀን ባፈሰስክባት ጊዜ... "መልአኩም ጽዋውን በላይዋ ላይ ባፈሰሰ ጊዜ፡ የ—የሰማዕታት ሁሉ ደም በውስጧ ይገኛል ብለሃል።"

6 ጌታ ሆይ፡ እርዳን... ጊዜው እያለቀ ነውና፡ አሁን መዘጋጀት እንድንችል አግዘን። ይህ ሁለት-ቀንድ ያለው አውሬ ከሰው ብዛት እና ከወገኖች መካከል ሳይሆን፡ ከምድር ሲወጣ ያየነው፡ "የበግ ቀንዶች ያሉት፡ ነገር ግን እንደ ዘንዶው የሚናገረው።" አባት ሆይ፡ እነዚህ አብያተ ክርስቲያናት አንዱ ከሌላው ጋር አንድነት ሲፈጥሩ፡ ሰዓቱ በደጅ እንደቀረበ እናምናለን፡ "ለአውሬው ምስልን እየሰሩለት ነውና"፡ ጌታ ሆይ፡ በዚያ ሕብረት የማጣመር መንጋ ሁሉ፡

እጅግ ከባድ ይሆንበታል። ዋናው ክልከላ ይመጣል፡ በዚያን ጊዜ ግን ቤተ ክርስቲያኔን እወስዳታለሁ ብለህ ቃል ገብተሃል። አሁንም እርዳን፡ ጌታ ሆይ።

7 እንዲት ጠብታ ከመዝነብዋ በፊት፡ ኖኅ መርከብ ውስጥ ገብቷልና። እሳቱ ሰዶም ላይ ከመውረዱ በፊትም፡ ሎጥ አምልጧልና። አባት ሆይ፡ የአቶሚክ ኃይላት ምድሪቱን ከማፈራረሳቸው በፊትም፡ ቤተ ክርስቲያን፡ እንደምታመልጥ እናምናለን። ጌታ ሆይ፡ ደስ ይለናል። ዛሬ ምሽትም፡ ቦምቦቹም አፈሙዝ ላይ ተንጠልጥለው፡ እንዳሉ ተገንዝበናል።

8 አይኖቻችን ወደ ሰማይ ሰናነሳውም እነሆ የሰው ልጅ ቤተ ክርስቲያኑን በንጥቀት ለመውሰድ ከዙፋኑ ተነሰቶ ወደ ምድር ሲያቀና ይታየናል፡ ያን ጊዜ ውድ እግሮቹ ኃጢአተኛዋ ምድር እንደማይነኩ እናውቃለን፡ ርብቃ ራሷ በግመል ላይ ተቀምጣ ከነበረችበት ከግመል ላይ ወርዳ፡ በአብራሃም ቤት መካከል፡ ባለው ሜዳ ላይ ሙሽራዋን አግኝታዋለችና። እግዚአብሔር ሆይ፡ እንዲሁ ቤተ ክርስቲያን ደግሞ ሙሽራችንን በአየር ላይ ታገኘዋለች፡ “እኛ ሕያዋን ሆነን የምንቀረው ያንቀላፉትን አንቀድማቸውምና። የእግዚአብሔር መለከት ይነፋል፡ በክርሰቶሰ የሞቱ አሰቀድመው ይነሣሉ፡ ጌታን (በሜዳ ላይ) በአየር ላይ ለመገናኘት ከእነርሱ ጋር እንነጠቃለን፡ ለዘላለም ከእርሱ ጋር እንሆናለን።”

9 አቤቱ፡ ጌታ ሆይ፡ ዛሬ ማታ፡ እርዳን። መራርነትን እና ግድየለሽነትን ሁሉ ውሰድልን፡ ለመንፈሳችንም ጣፋጭነትን ሰጥ፡ ከቅዱሰ መንፈሰ ጋር **እጅግ** መቅለጥ ይሁንልን። ዛሬ ማታ የእግዚአብሔር መልአክ ይግዛን።

10 ጌታ ሆይ፡ ለዚህ ህዝብ ምን ማለት እንዳለብኝ አላውቅም። እንግዲህ፡ አንተ የሰራኸው ታሪክ እና ሌሎች ነገሮችን ጽፌ ይዣለሁ፡ የወደፊቱን መተርጎም ግን የአንተ ነው፡ ሰለዚህ በኢየሱሰ ክርሰቶሰ ሰም እንድትሰጠን እጸልያለሁ። ኣሜን።

11 አሁን ሁላችንም የራእይ መጽሐፍ እንከፍታለን። ዛሬ ማታ የደረሰንበት ይህ የቤተ ክርስቲያን ዘመን... አራተኛው የቤተ ክርስቲያን ዘመን፡ ትያጥሮን፡ የጨለማው ዘመን በመባል የሚታወቀው ታላቅ የቤተ ክርስቲያን ዘመን ነው። ይህ የቤተክርሰቲያን ዘመን ከ606 ጀምሮ 1520 የሚያበቃ ዘመን ነው። ይህን... ለመምረጥ፡ የቻልኩትን ያህል ጥሬአለሁ። ብዙ ምሁራን—ኮከቡ ቅዱስ ፓትሪክ ነው ይላሉ... እያንዳንዳቸው...

12 **ሰባቱ ከዋክብት** የሰባቱ ቤተ ክርሰቲያን ዘመናት “ሰባት መላእክት” ናቸው። የነገ ምሽት፡ ሉተር፡ ከዚያም ዌሰሊ መሆናቸውን፡ ያለ አንዳች ጥርጣሬ እናውቃለን። የሎዶቅያ ቤተ ክርሰቲያን ኮከብ ማን እንደሚሆን አናውቅም። ብቻ ግን... በዚያ ዘመን እንገኛለንና፡ ጊዜውም ከጴንጤቆሰጤ ጅማሬ ከ1906 ወዲህ ነው። ዶግማዎችን ሁሉ ገለባብጦ የሚያጠፋ፡ እና ቤተክርሰቲያን ወደ ቤቷ እንድትሄድ የሚያዘጋጃት መልአክ ይነሣል። አሁን፡ እነዚህ አንዳንድ በ—በ... መንፈሰ፡ በምልክቶችና በድንቆች የሚነሣ ይሆናል። አሁንም፡ ይህን እንድናውቅ እግዚአብሔር እንዲረዳን እጸልያለሁ።

13 ይሄኛው በምመርጥበት ጊዜ፡ በደንብ ሳይ፡ ቅዱሰ ፓትሪክ በጣም ታላቅ ሰው ነበር። አንዳንድ ጥንታውያን ጽሑፎችን ሳያቸው፡ ቅዱሰ ፓትሪክ ካቶሊክ አልነበረም። የካቶሊክ ቤተ ክርሰቲያንን ተቃውሟል። በተሃድሶ ወቅት፡ ዶግማዎቻቸው ሁሉ ተቆፍሮ በተገለባበጠ ጊዜ፡ ቅዱሰ ፓትሪክ የካቶሊክ

ቤተ ክርስቲያን መቃወሙን ተረጋግጧል። እና... ቅዱስ ፓትሪክ ድርጅታዊ ሰው ነበር፡ የራሱ ትምህርት ቤትም ነበረው። በመጀመሪያ... ከባሕር ዳርቻ ታፍኖ በተወሰደ ጊዜ፡ ከእርሱ ጋር፡ ሁለት ታናናሽ እህቶቹ ነበሩ ከዚያ ወዲያ ግን ስለ እህቶቹ ሰምቶ አያውቅም ነበር። ምናልባትም ወደ ሮም ተወሰደው፡ ለባርነት ተሸጠው ይሆናል። እርሱም ተወስዶ ለባርነት ተሸጦ እሪያን የመጠበቅ ሥራ ተሰጠው።

14 እሪያዎቹን ለመጠበቅ—እና ለማሰማራት፡ ውሾች ያሰለጥን ነበር፡ እርሱ በሚያሰማቸው የተለያዩ ድምጾች እና ልዩ ልዩ ነገሮች ይመጡለት ነበር። በመጨረሻም በጀልባው ኋለኛው ክፍል፡ የማምለጫ መንገድ አድርጎ ተጠቅሞበታል፡ ወደ ባሕር እስኪወጣ ድረስ፡ ውሾቹ ይሸፍኑት ነበርና። በኋላ ወደሚወዳት አገሩ ወደ አየርላንድ መጣና፡ እናቱ እና አባቱንም፡ በህይወት አገኛቸው። ቅዱስ ፓትሪክ—የታላቁ ሰው የቅዱስ ማርቲን የእህት ልጅ ነው።

15 ይህም፡ ቅዱስ ማርቲን ከኢየሱስ ክርስቶስ ጀምሮ ከታዩ ታላላቅ ሰዎች፡ በዋናዎቹ ተርታ የሚሰለፍ ታላቅ ሰው ነበረ። አብያተ ክርስቲያኖቹ ሁሉ በመንፈስ ቅዱስ የተሞሉ፡ ሁሉም በልሳኖች የሚናገሩ፡ ምልክትና ድንቆች፡ ተአምራቶች፡ እና ልዩ ልዩ ተአምራቶች የሚፈጸምባቸው ነበሩ። ቤተ ክርስቲያን ከካቶሊካዊነት ጋር በተጋባችበት ዘመን ላይ የጴንጤቆስጤን እምነት የጠበቀ ሰው ነው፡ አረማዊነት እና ኒቆላውያን በአንድነት በመጋባት፡ ድርጅት የፈጠሩበት፡ ኒቆላውያን—የፈጠሩት፡ **ኒቃኦ** ትርጉሙም፡ ምእመናንን "መውረር፡ መውረር፡ ወይም መጣል፡" መንፈስ ቅዱስን፡ ከጉባኤው ማስወገድ፡ "ካህኑ ብቻውን ቅዱስ፡ እና ጻዲቅ ሰው ነው" የተባለበት። አያችሁ? ብቻ፡ በካህን ፊት ኃጢአታቸውን ይናዘዙ እንጂ፡ ሌሎች እንደፈለጉ የሚኖሩበት ህይወት ነው። ከዚያም...

16 የመጀመሪያውን ቢሾፕ፡ ማቆማቸውን—ቆስጠንጢኖስ መሾሙን፡ ትናንት ማታ አይተነዋል፡ እርሱም... እነዚህን ህጻዎች ሰጣቸው፡ አሁን ያያችኋቸው ነገሮች እስከነ ቀናቸው ሰጥተናችኋል። ከዚያም በታኅሣሥ 21 ቀን፡ ጸሐይ ቶሎ የምትጠልቅበት የዓመቱ አጭሩ ቀን ውስጥ የሚያከብሩት፡ ታላቅ በዓል ነበራቸው። ያን ጊዜም፡ እርሱ "ሰን ዴይ" ነው የሚሉትን፡ ታላቁን ኑፋቄ አስገቡ። አያችሁ፡ ሚያዝያ ላይ የነበረው የኢየሱስ ክርስቶስ ልደት ወደ ታኅሣሥ 25 ቀን፡ ወደ—ጸሐይ የልደት ቀን ላይ አወረዱት።

17 ታኅሣሥ 25 ቀን። በእነዚያ አምስት ቀናት ውስጥ ሮማውያን ትልቅ ክብረ በዓላቸውን፡ የሰርከስ ትርኢት፡ እና የመሳሰሉትን ያደርጉበት ነበር፡ ይህም ታላቅ የሆነ አረማዊ ድግስ የሚያደርጉበት ጊዜ ነበር። ይህ ሰው እንደ አምላክ አድርገው በዚያ ጊዜ ሾሙት፡ በብዙ አሸንክታብም አለበሱት። ይህም አምላካቸው በጎናቸው መሆኑ ነው። እና ይህም ለእነርሱ... የድኅረ-ሺህ አመት መንግስት ሰዎች መምጣት፡ ያኔ ነው፡ የቤተ ክርስቲያን የሺህ አመት መንግስት ዘመን ውስጥ እንደገቡ ይመስላቸው ነበርና። ምክንያቱ፡ ምንም የማያስፈልጋቸው፡ ባለጸጎች ነበሩ፡ መንግስት እና ቤተ ክርስቲያን ተጋብተዋል። "የሺህ አመት መንግስት ሆኗል፡" የሚል ትምህርት እስከ ዛሬ ድረስ የካቶሊክ ነው። አያችሁ? አሁን፡ "የሺህ አመት መንግስት ሆኗል፡" የሚለው ነገር ስሕተት እንደሆነ እናውቀዋለን። የሺህ አመት መንግስት፡ የሺህ አመት መንግስት የሚያስመጣው የክርስቶስ ዳግም መምጣት ነው። በትክክል።

ስለ ነጻነት ቀን መምጣት፡ ምድር ታለቅሳለች፡
ጌታችን ዳግም ወደ ምድር የሚመጣባት ወቅት።

18 እንግዲህ፡ ይሄኛው ታላቅ ቅዱስ ሰው ኮሉምባ ይባላል። ታላቅ የእግዚአብሔር ሰው ነበር።

19 አሁን፡ ታሪኩን ጽፌ ይዤዋለሁ። በመጀመሪያ ግን፡ አራተኛው የቤተክርስቲያን ዘመን **ትያጥሮን፡** ማለት “ልል፡ ልቅ፡” ወይም፡ “ጭጋጋማ፡” ማለት ነው። እያችሁ? ከ 606 እስከ 1500 ድረስ የነበረ ጋጠወጥ ዘመን ነው።

20 ኮከቡም ከአየርላንድ እና ከስኮትላንድ የመጣው፡ ኮሉምባ ነበር፡ እርሱም የቅዱስ ማርቲን የእህት ልጅ ነበር፡ ከቅዱስ ፓትሪክ ከሰልሳ አመት በኋላ የነበረ፡ ስለዚህ አገልግሎቱ የሚጀምረው ከቅዱስ ፓትሪክ፡ ከሰልሳ አመት በኋላ ነው። እሱም...

21 የሮማውያንን ትምህርት ፈጽሞ አልተቀበለም። ታላቅ የእምነት ሰው ነበር። የሮማውያንን ትምህርት ተቃወመ፡ ወደ ሮም አልሄደም፡ ሙሉ ለሙሉ ተቃወመ። እርሱን በቀኖና ያጸደቁበት ሰፍራ አይታየኝም፡ እንጃ። እንደ ቅዱስ ማርቲን እና እንደ ሌሎቹ፡ እርሱንና ኢራኔዎስን በቀኖናቸው አልተካተቱም ምክንያቱ የጴንጤቆስጤ ምልክቶችና ድንቆች በሚታይባት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ስለነበሩ፡ ስለሚያምኑ ነው። የሮማውያንን ትምህርት፡ አስተምህሮአቸውን ፈጽሞ አልተቀበለም። መንፈሳዊ የነበረችውን እናቱ ተከትሎ ትምህርቶቹ ሁሉ ከመጽሐፍ ቅዱስ አደረገ፡ እሷም የቅዱስ ማርቲን እህት ነበረች፡ እና የሮማውያንን ትምህርቶች መቼም አልተቀበለም። የማርቆስ 16 ምልክቶች እያንዳንዱን አማኝ መከተል እንዳለባቸው አስተማረ። አሜን! እኔ... የምወደው ዓይነት ሰው ነው፡ አማኝ የሆነ። አዎን፡ ወዳጄ።

22 የሚጣራ የእግዚአብሔር ድምጽ በጆሮው––ሰምቷል። ይህም ለእርሱ ሌላኛው ትልቅ ምልክት ነበረ፡ እያችሁ። ከዚያ በኋላ ምንም ነገር ሊያሰቆመው አልቻለምና፡ ቀጠለ፡ ኧህ-ሃህ፡ ኧህ-ሃህ፡ የእግዚአብሔርን ድምፅ በጆሮው የሰማው ጉዞ ላይ ሆኖ ነበረ።

23 ከተአምራቶቹ አንዱ... በርግጥ ጽፌ የያዝኳቸው-... አሉኝ፡ ምሳሌ ለመውሰድ ያክል ግን። አንደኛው ተአምሩ ጌታ ወደላከው ወደ አንዲት ከተማ ደረሰና፡ ከተማይቱም ልትቀበለው አልፈለገችም፡ እና ወጥተው ሙዚቀኞችን በመጥራት... ይዘው መጡ፡ እና ደግሞ፡ ደጆቹን ሁሉ ዘጋግተው፡ ሙዚቀኞች እንዲጫወቱ በማድረግ ልቡን ሊገዙ ሞከሩ። እርሱ ግን ሰብከቱ ጀመረ፡ የሙዚቀኞቹን ልብ ገዛና ደጆች ሁሉ ተከፋፈቱ፡ እርሱም ገብቶ፡ ሰበከላቸው። ሰዎቹን ሁሉ ቀየራቸው።

24 በተጨማሪም መናገር የምፈልጋት ትንሽ ነገር ይህች ናት። ወደ አንዲት ከተማ ሄደ። እና እንደሚታወቀው፡ በዚያ ዘመን ከተሞቻቸው በግድግዳ የታጠሩ ነበሩ። እና ወደ ከተማይቱ ደርሶ፡ እናስገባህም አሉት። መመለስ ጀመረ፡ ያን ጊዜ የከተማይቱ አለቃ ልጅ በጸና ታመመ፡ እና ሰዎችን ወደዚህ መልካም ሰው መልእክተኞችን ከኋላ ላኩበት። ተመልሶ መጥቶ በሟቹ ልጅ ሰውነቱ ላይ ተኛበት፡ እና ወደ ሕይወት ተመለሰ።

25 ቤተ ክርስቲያኑ በመንፈሰ ቅዱስ የተሞላች ነበረች፡ እያንዳንዱ የቤተክርስቲያኑ አባል፡ በመንፈስ ቅዱስ መሞላት ግዴታው ነበርና አንዳች

አይጎድልባቸውም ነበር። የሮምን የስልጣን ተዋረድ እጅግ ይጠላው እና ይቃወም ነበር። የዘመኑ ኮከብ እርሱ እንደነበረ አምናለሁ። ምን ያደርግ ነበር? በልሳኖች ይናገራል፡ በጌታ በኢየሱስ ስም ያጠምቃል፡ ያኔ የጀመሩትን ይፈጽም ነበር። እግዚአብሔር ፍጻሜ የሌለው ከሆነ፡ ቤተ ክርስቲያን ስትቋቋምም ከመጀምሪያ በዚህ መንገድ ከነበረ፡ እንዲሁ መቀጠል ይኖርባታል፡ (በታናሺቱ መንጋ ሳይቀር) እንዲሁም ሆኗል፡ በሉተር እንደገና ካንሰራራችበት ጊዜ ጀምሮ፡ ከመላ ጎደል እስከተጣበበችበት **አሁን** ድረስ ያው ናት።

26 ስለዚህ፡ አሁን እንጀምር፡ እና ከእነዚህ ጥቅሶች አንዳንዶቹን ማውጣት ከቻልን እናያለን፡ ከ... ከ18ኛው ቁጥር እንጀምራለን፡

**... በትያጥሮን** ወዳለው **ወደ ቤተ ክርስቲያን መልአክ እንዲህ ብለህ ጻፍ፡...**

27 እነዚህ ለማን እንደተጻፉ—አስተውላችኋል? መልእክቶቹ የተጻፉ ለመልአኩ ናቸው፡ ወይም የቤተ ክርስቲያኒቱ ዘመን ብርሃን ለሚያመጣ ለአገልጋዩ ነው። አያችሁ? ትናንትናም፡ ጴርጋሞን በተባለች የ—የቤተ ክርስቲያን ዘመን መዝጊያ ላይ፡ አይተነው ነበርን፡ ማለት የቤተ ክርስቲያኒቱ መልአክ (ይሄኛው ቤተ ክርስቲያኒቱን ዘመን ድል በማድረጉ) የሚቀበለው ድንጋይ እንደሚኖር። እና በዚህ ድንጋይ ውስጥ...

28 እንግዲህ፡ "ድንጋይ" ወሰደን ተምሳሌታዊ እንዳደረግነው፡ ትርጉሙ "ዓለት" ማለት ነው። ምንድነው? መልአኩ "ድንጋይ" እንደተባለው፡ እንደ ጴጥሮስ ይሆናል።

29 ስማችሁ በህይወታችሁ ላይ ተጽዕኖ እንዳለው ተምረናል። አሁን፡ ወደዚያ ብዙም አልዘልቅም፡ ዲያብሎስም የተሳሳተ የቁጥር ስሌት እንደሚጠቀም፡ እናውቃለን፡ በሰዎች **ስሜት**፡ እና በመሳሰሉት ነገሮች ጀምሮ፡ ወደ መናፍስታዊነት ይቀይረዋልና። መናፍስታዊነትም ከዲያብሎስ ነው። እናውቀዋለን። መመልከት የሚገባችሁም፡ በዚህ መንገድ ነው። እነርሱ...

30 ኢየሱስ "ብዔልዜቡል፡" ነው "ዲያብሎስ" ነው ያሉበት ምክንያት፡ አያችሁ፡ ምክንያቱ፡ የተሰወረውን የልባቸው አሳብ ስለሚመረምር ነው። አያችሁ፡ እሱ ግን የእግዚአብሔር ቃል ነበረ። ዕብራውያን 4 ሲናገር፡ "የእግዚአብሔር ቃል፡ ሁለት-አፍ ካለው ይልቅ የተሳለ ስለታም ሰይፍ ነው፡ የልብንም ስሜትና፡ የአእምሮ አሳብ ይመረምራል።" አያችሁ? ስለዚህ፡ እርሱ ቃል ነበረ፡ ሕያው ቃል እርሱ ነው፡ ሕያው ቃልም ወደ እኛ ይመጣል በእኛም ተመሳሳይ ስራ ያደርጋል። አያችሁ፡ ተመሳሳይ ነው፡ ቃሉም ያው ነውና። አያችሁ፡ በእኛም ያው ነው። መንገዱ ያ ነው። እና አንዳንድ ጊዜ በዚያ ቅንፍ ውስጥ የሌሉ ሰዎችም በልሳኖች ይናገራሉ፡ ሌላው ደግሞ ይተረጉመዋል። ያ ምንድነው? ቃል በእኛ መካከል እንደገና ስጋ ሲሆን ነው።

31 ከዚያም፡ እንግዲህ ይህ መልአክ... "ድንጋይ" የምትቀበለው ቤተ ክርስቲያን ዘመን መልአክ ይህን የሚቀበለው ነገር እንዳለ አስተውለናል። ይህም **ነጭ** ድንጋይ ነው፡ ይህ ማለት የራሱ ጽድቅ ማለት አይደለም፡ "የእግዚአብሔር ጽድቅ" እንጂ።

32 በድንጋዩ ላይም "ስም" ነበረው፡ ስሙም ከተቀበለው በቀር ማንም አያውቀውም። የተቀበለው ያውቀዋል፡ ከእርሱ በቀር ግን የሚያውቅ የለም።

ታዲያ እነዚያ እኔ እከሌ ነኝ የሚሉትን ሽንገላቸውን፡ ሲጎሰሙባችሁ፡ እኔ "ዮሐንስ" ነኝ፡ እኔ "ጳውሎስ" ነኝ፡ እኔስ "ማርያም" ነኝ፡ እኔ "**ይህ**፡" "**ያ**፡" እና "**ሌላ**" ነኝ ሲሉ። አትመኗቸው፡ ቢሆኑ ኖሮ፡ እንዳች መናገር ባላስፈለጋቸው ነበርና። እያችሁ? ትክክል። ለራሱ ብቻ መያዝ አለበት። እራሱን ያውቃልና። እሱ ራሱ ብቻ እንጂ ሌላ አያውቀውም፡ እሱ ግን ያውቃል ምክንያቱ ድል የነሣ ሁሉ በ—በ—በዚህ መንገድ አዲስ ስም ይቀበላልና።

33 አብርሃም ስሙ አብራም ይባል እንደነበር አስተውላችኋል፡ እግዚአብሔር ሊጠቀምበት በመጣ ጊዜ ግን፡ ስሙ "አብራሃም" አለው። ሦ-ራ-ይ ስሟ ሦ-ራ-ይ ነበረ፡ እግዚአብሔር ሊጠቀምባት በወደደ ጊዜ ግን፡ ስሟ ሳ-ራ-ህ፡ **ሳራህ** "ልዕልት" አላት። ያዕቆብን... ታውቃላችሁ? **ያዕቆብ** ማለት "አታላይ" ነበረ። **ኤሳው** "ቀይ" ማለት ነው፡ ፀጉራማ እና ቀይ ነበረ፡ ዔሳው፡ ባለ ቀይ-ራስ፡ ሁለመናው ቀይ ነው። እንግዲህ **ያዕቆብ** ማለት "አታላይ" ነው። **አታላይ** ማለትም "የሚያታልል" ማለት ነው። ኤሳውም አለ፡ "'አታላይ' ነው፡ ስሙስ **ያዕቆብ** አይደለምን?" ሌሊቱን ሙሉ ከጌታ ጋር ታግሎ፡ ካሸነፈ፡ እና ከተባረከ በኋላ ግን፡ እግዚአብሔር ስሙን ለወጠለት፡ ያዕቆብን "ልኡል ከእግዚአብሔር ጋር" ሲል፡ **እስራኤል** አለው፡ ጳውሎስም መንፈስ ቅዱስን በብርሃን አምሳል በርቶ እስኪያገኘው ድረስ **ሳውል** ተብሎ ይጠራ ነበር፡ ስሙ ከሳኦል ወደ "ጳውሎስ" ለወጠለት። ስምዖንም ኢየሱስን ባገኘው ጊዜ ስሙ "ጴጥሮስ" ለወጠለት። ያም...

34 ኢየሱስ ድል በነሣ ጊዜም፡ ስሙ ተለወጠ። ያን ስሙንም ይገልጣል፡ "እርሱ ድል እንደነሣ፡ ድል ለሚመሣ ሁሉ፡ አዲስ ስም ይቀበላል፡ አዲሱን ስሜን እገልጥለታለሁ።" እያችሁ? ድል አድራጊ ሁሉ፡ ስል፡ ከእነዚያ፡ ዋናዎች እና ሌሎች ማለት ነው። አሁን፡ በርግጥ፡ የእስራኤል ልጆች ሁሉ ሰማቸው አልተለወጠም። በትክክል። ዋናዎቹ አለቆች ግን፡ ድል በነሡ ጊዜ፡ አዲስ ስም ተቀብለዋል። እንዴት እንደሚተሳሰር እያችሁት? ፍጹም ነው።

35 ሌላውም "የተሰወረ መና" እንዳለውም አይተናል። እንግዲህ የተሰወረ መና፡ የኅብስቱ ምሳሌ ነው። ኅብስት የካህናቱ ብቻ ድርሻ ነበር። በትክክል። ኅብስት ለካህን ብቻ ነበረ። እነርሱም... አለቆች፡ ናቸው፡ ለካህኑ የሚዘጋጅለት ልዩ ነገር ነው፡ እርሱም ድል አድራጊ ነው። ጉባኤው በሙሉ መና ይበላል፡ እሱ ግን **የተሰወረውን** (የተለየ) **መና** ይበላል፡ ወይም "**ልዩ መገለጥ**፡" ይህም፡ ኢየሱስ ማን እንደሆነ፡ እና ስለ እሱ፡ ከሞላ ጎደል ስለ እሱ ማወቅ ነው። እያችሁ፡ ድል የሚነሣ መገለጡን ያገኛል። ለመልእኩ፡ "ስለዚህ፡ አጥብቀህ ያዝ... " ድል ስለነሣ ነው። ለቤተ ክርስቲያኑ **መልእክ** የተባለለት ይህ ነው። እያችሁ?

36 አሁንም ዛሬ ማታ፡ የምንጀምርበት፡ ይህ ይዘናል፡

> **... በትያጥሮን** ወዳለው **ወደ ቤተ ክርስቲያን መልአክ እንዲህ ብለህ ጻፍ፡ የእግዚአብሔር ልጅ እንዲህ ይላል፡ የእሳት** ነበልባል**... ዓይኖች፡ እግሮቹም... እንደ ብርቱ ናስ...** የሆነው፡

37 እንግዲህ፡ በራዕይ መጀመሪያ፡ ወይም በኤፌሶን ዘመን፡ መጀመሪያ ባየነው ጊዜ፡ በሰባት መአዝናዊ የክብር ሰብእናው አይተነዋል። "ጸጉሩ... " በጌታ ቀን ዮሃንስ እሱን ማየቱን እናያለን።

38 ምድር ላይ፡ ነብይ ነበረ፡ የእግዚአብሔር ነብይ ነበረ፡ አሁን ሲመጣ፡ ካህን ነው። የገዛ ደሙን ይዞ ወደ አብ ሄዷል፡ ይህም ካህን ያሰደረገው። ሲመጣም ንጉሥ ይሆናል። ነቢይ፡ ካህን እና ንጉስ። የእግዚአብሔር ነቢይ፡ ንስር ነበር። የእግዚአብሔር ካህን፡ በግ ነበር። ተመልሶ ሲመጣ፡ አንበሳ፡ ንጉሥ ይሆናል፡ (በይሁዳ ነገድ) ይነግሣል።

39 በክህነት አገልግሎቱ መካከል ግን፡ ከመቅደሱ ሲወጣ፡ በዚያ ቆሞ እናገኘዋለን። ዮሐንስ "በጌታ ቀን" በመንፈስ ነበርኩኝ አለ፡ በሰባተኛው ቀን፡ ወይም በእሁድ አይደለም፡ ሁለቱም ስሕተት ናቸው። ከመጽሓፍ ቅዱስ መርምረን እንዳገኘነው፡ የጌታ ቀን፡ እንደነበረ ደርሰንበታል። ይህም የሰው ቀን ነው። የጌታ መምጣት ለእርሱ ቀኑ ይሆናልና።

40 እና በጌታ ቀን ውስጥ እናየዋለን። ጌታን ባየው ጊዜም፡ "ጸጉሩ እንደ በረዶ-ነጭ፡" ነበረ። ይህም ፈራጅ እና ዳኛ ስለመሆኑ ያስረዳል።

41 ሌላው ደግሞ፡ በዚያን ጊዜ ካህን አይደለም፡ ካህን የሚታሰረው በወገቡ ነው፡ ትርጉሙም **አገልግሎት** ነው። ነገር ግን እዚህ ጡቶቹ ዙርያ ላይ፡ ከፍ **እርጎ** ታጥቆ ነበር፡ ይህም ማለት **ዳኝነት** ነው። አሜን! በሰባቱ የወርቅ መቅረዞች መካከል ሲመላለስ አይተነዋል።

42 እና ይህም "ጥንት ወደ ሸመገለው" ይወስደናል፡ በነጩ ዙፋን ፍርድ ፊት ዳንኤል ያየው **ነጭ** ስለ መሆኑ፡ "ጸጉሩ እንደ በረዶ ነጭ ወደ ነበረው በዘመናት ወደ ሸመገለው መጣ።"

43 አሁን፡ "ነጭ።" ድሮ የእንግሊዝ ዳኞች፡ ወደ ፍርድ ወንበር በሚወጡ ጊዜ፡ ዳኞች ስለሆኑ፡ ትልቅ ነጭ ዊግ፡ ነጭ እንደ-በረዶ ዊግ ራሳቸው ላይ ያጠልቁ ነበር። ዮሐንስም በጌታ ቀን፡ ዳኛ ሆኖ አየው። አሜን!

44 እዚህ ጋር አሁን "እንደ እሳት ነበልባል የሚመስሉ ዓይኖች እንደነበሩትም" ሆኖ እናገኘዋለን። አንዴ የሰው እንባ ያቀረሩ አይኖች... አሁን የእሳት ነበልባል አይኖች ናቸው። ከአምስት ደቂቃ በኋላ ከሞት እንደሚነሳ እያወቁ፡ ዓይኖቹ በሞተ ሰው ፊት ቆመው ሊያነቡ ይችላሉ፡ ይህም የሰው ርህራሄ ብቻ ነው። ከዚያ በስተጀርባ ግን ዘልቆ የሰው ህይወትን የሚመረምርበት እና ሰውየው ማን እንደሆነ ህይወቱን በጥልቀት መናገር የሚችልበት ኃይል ነበረ። ምክንያቱ አሁን አመጣጡ በእሳት ነበልባል ነጸብራቅ ነው። በምድር ሁሉ ከፊት ከኋላ የሚመለከቱ፡ የሚሆነውን ሁሉ የሚያዩ አይኖች ናቸው። በፍርድ ቀን የት ትቆማላችሁ? ኃጢአቶቻችሁ በፊቱ የተራቆቱ ይሆናሉና።

45 ሌላው "ከአፉም፡ በሁለት-ወገን የተሳለ—ስለታም ሰይፍ፡" እንደወጣ አስተውላችኋል፡ ይህም **ቃል** እንደሆነ ተረድተናል።

46 እግሮቹም "የጋለ ናስ፡" እና ሌላ ሆኖ አይተናል፡ ይህም "የተመሰረተበት መሰረት" ነው። ሁሉን የሚችለውን የእግዚአብሔር የቁጣ ወይን መጥመቂያ ረግጦ፡ ካደቀቀው በኋላ ኃጢአትን በራሱ ላይ ወሰደ፡ ዙርያውን ተረጭቶ ወጥቶ፡ ጌታን ደስ አሰኘ። ትክክል። መሰረቱም መሰረታችን ነው፡

በጠንካራው ዓለት፡ በክርስቶስ ላይ፡ ቆሜያለሁ፡ (አለ
ኤዲ ፔሮኔት፡)
ሌላው ሁሉ የሚያሰምጥ አሸዋ ነው። (በትክክል።)

47 አሁን እዚህ ላይ፡ በእያንዳንዱ የቤተ ክርስቲያን ዘመን በመጣ ቁጥር፡ በአምላክነት ሰሞቹ በአንደኛው ይገለጥለታል። ወደ ኋላ ተመልሰን እንደምናየው፡ ከመገለጦች ሁሉ የመጀመሪያ የሚሆነው መገለጥ ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ ስለመሆኑ (ሉዓላዊ አምላክነቱ) ነው፡ “የነበረ፡ ያለው፡ የሚመጣውም እኔ ነኝ። ፊተኛውና፡ መጨረሻው፡ ሁሉን ቻይ አምላክ እኔ ነኝ።” እያችሁ፡ የመጀመሪያ መገለጥ ይህ ነው። የሚናገረውን ለማየት ዮሐንስ ዞረ። እርሱን ባናገረው ጊዜ፡ የመጀመሪያው ነገር...

48 ነገስታት ሁሉ፡ ሲናገሩ፡ ማንም ይሁን፡ መጀመሪያ ሰ—ሰለ—ማንነቱ ይናገራል። “እኔ ከእናንተ ጋር ስነጋገር፡ ስለማታውቁኝ **እከሌ-እና-እከሌ** እባላለሁ። ዊልያም ብራንሃም እባላለሁ፡ **ጆን ዶዊ** እባላለሁ፡” የየራሱን ያስተዋውቃል።

49 “ፊተኛውና መጨረሻው እኔ ነኝ፡ ሕያው የነበረውና የሞተው፡ ለዘላለም ሕያው ሆኖ የሚኖረው እኔ ነኝ፡” አለ። ኦህ፡ ማይ! አምላክነቱ። እዚህ ጋር ከሰባት መአዝናዊ የክብሩ መገለጫዎች እናየዋለን። እያንዳንዱን የቤተ ክርስቲያን ዘመን—እራሱን በልዩ ልዩ የአምላክነቱ መገለጫዎች፡ በልዩ ልዩ መከበሪያ መዓርጎቹ አስተዋወቃቸው።

50 አሁንም፡ ዛሬ ማታ፡ እንደሚነድ እሳት ሆኖ መጥቶ። ወደ ሎዶቅያ... ማለቴ ወደ ትያጥሮን ቁልቁል እየተመለከተ ነው። ቤተ ክርስቲያን ከካቶሊክ እና ከጣዖት አምልኮ ጋር የተጋባችበት ዘመን፡ ወይም ኒቆላውያን እና ጣዖት አምልኮ ተጋብተው የተደራጀውን፡ የመጀመሪያ ቤተ ክርስትያን የወለዱበት ዘመን ነው።

51 እግዚአብሔርም (በኤፌሶን ስለ ነበረው) የኒቆላውያንን ***ሥራ***፡ በ—በትንሿ የጴርጋሞን ቤተ ክርስቲያን ውስጥ “ትምህርት” እንደሆነ፡ ይህም “የበልዓም ትምህርት” መሆኑን ተናግሯል። በለዓምም የእስራኤል ልጆች ወደዚያ ወርደው እንዲያመነዝሩ ያስተማረ፡ ወይም ከሞዓብ ጋር (ለብ ካሉት የቤተ ክርስቲያን አባል ጋር) ከመደበኛው ቤተ ክርስትያን፡ ወይም ከታላቁ ድርጅት ጋር፡ እንዲሴስኑ ያሰደረገ ሰው ነው። እግዚአብሔርም የተናገረው፡ የኒቆላውያን አስተምህሮ እንደሆነ እናየዋለን... እና... ኃይሉን ሁሉ በቤተክርስቲያን ውስጥ አሰቀምጠና ተመቻችታ የተቀመጠች ድርጅት አደረጋት፡ እርሱም “አንተ ደግሞ የጠላኸውን፡ እኔም ጠልቼዋለሁ፡” አለው። “ጠልቼዋለሁ! ጠልቼዋለሁ! ጠልቼዋለሁ!” እያለ ይቀጥልና፡ **እዚህጋ** ወደ ጠርዝ ደረሰ። **እዚህ** ጋር ቤተ ክርስቲያን እጅግ አነሰተኛ እሰክትሆን ድረሰ፡ ምን ያህል እንደተጣበበች ተመልከቱ፡ እኛ አሁን ያለንባት ቤተ ክርስቲያንም ይህች ናት።

52 እንግዲህ፡ ይህ መገለጥ ለዚህች ቤተ ክርስትያን፡ በመጣ ጊዜ፡ ሮም በአካባቢዋ ባሉ ታላላቅ ድንጋዮች ላይ ከሳርና ከገለባ፡ የገነባችበት ጊዜ ነበር። አሁን ለዚህች ቤተ ክርስቲያን እየተናገረ ባለው ጊዜ ግን “አሁንም ጊዜን አልፎ የሚያይ የእሳት ነበልባል ሆኖ ይቀጥላል፡ መሰረቱም፡ እጅግ በጋለ እቶን የተፈተነ፡ ጠንካራ ናስ ነው እንጂ፡ ሳር እና ገለባ አይደለም።” መሰረቱ የጸና ነው። ይህ ደስ ይለኛል። ምን ላይ እንደቆምን እናውቃለን።

53 እሺ፡

> **ሥራህን፡** እና **ፍቅርህንም፡ አገልግሎትህን፡ እምነትህንም አውቃለሁ፡ ትዕግሥትህንና፡ ሥራህን፡ እና ከፊተኛው ሰራህ ይልቅ—የኋለኛው እንዲበዛ አውቃለሁ።**

54 እሺ፡ ቤተክርስትያኒቱ በመጠኑ እየተንገዳገደች፡ ከሞላ ጎደል የተቆረጠች መሰላለች፡ እና ከታላላቅ መንፈሳዊ ጉባኤዎች ርቀው፡ በሰራዎቻቸው ላይ መታመን ጀምረዋል። እግዚአብሔር በሥራ ላይ እንድንታመን አይፈልግም።

55 ሰርዓት የመሆን ምልክት—ይህ ነው። "ወይዞሮ ጆንሰብ በአንዲት እንጨት እንይዛታለን። **እከሌ-እና-እከሊትን፡** እና ልጆቻቸውን፡ በጥቂት ጨርቆች እንይዛቸዋለን።" ያም ምንም አይደለም። ይሁን እንጂ፡ አትመኩበት፡ እንዲህ አታድርጉ። ወንድሜ፡ ያ—ያ—ያ መልካም ሰራ ነው፡ መልካም፡ እና ጥሩ ዜጋ የሚያደርገው ነገር ነው። ክርስቲያን ለመሆን የሚያስፈልገው ግን የዳግም-መወለድ ልምምድ፡ እና የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ነው። እሺ።

56 ጊዜ እየሄደ በቀጠለ ቁጥር፡ በፍቅር እና በእምነት ፈንታ፡ ሰራን በመተካት ከጊዜ ወደ ጊዜ መንገዳገዳቸውን ቀጠሉበት።

57 እሺ፡

> **ሥራህን** አውቃለሁ፡... **እምነትህን** አውቃለሁ፡ **ትዕግሰትህን** አውቃለሁ፡ **እና** ወዘተ...

58 አሁን ግን 20ኛውን ቁጥር እናነባለን፡ ይህን ሰሙት፡

> **ዳሩ ግን ነቢይ ነኝ የምትለውን፡ ባሪያዎቼንም እንዲሴሰኑና፡** ለጣዖት **የታረደውን እንዲበሉ፡ የምታስተምረውን**ና... **የምታስተውን ያችን ሴት ኤልዛቤልን፡ ሰለምትተዋት የምነቅፍብህ ነገር አለኝ።**

59 እሺ፡ "ሴት።" ትናንት ማታ **ሴት** የምን ምሳሌ እንደሆነች አይተናል? የ "ቤተ ክርስቲያን።" እንግዲህ፡ አሁን "ኒቆላውያን" ተብለው መጠራታቸውን አይተናቸዋል፡ "የበልዓም ትምህርት" ነበረ፡ አሁን ግን "ኤልዛቤል" ሆኗል።

60 እሺ፡ "ኤልዛቤል።" ካስተዋላችሁት፡ ታላቁ ታሪክ ይህ ነው። አሁን፡ ማስታወሳ መያዝ ከፈለጋችሁ፡ ከአንደኛ ነገሰት ጀምሩ፡ ከ... አንደኛው ነገሰት፡ ከ 16 ጀምሮ። ኤልዛቤል የአብርሃም ልጅ፡ ወይም የእነዚህ፡ የአረማውያን የሮም ልጅ አልደለችም። ኒቆላውያን ከእውነተኛ ክርስቲያኖች፡ ራሳቸውን ያገለሉ ቀዝቃዞች እና መደበኛ ክርስትያኖች ናቸው፡ "እምነቱንም ረሰተውታል።" ቤተክርስትያኒቱን የድግስ ቤት ሊያደርጓት ይፈልጋሉ፡ ልክ አሁን እንደሆነው አይነት፡ በውሰጧ ምንም መንፈስ የሌላት፡ እንደ ድግስ ቤት ሊያደርጓት፡ "የተአምራት ቀናት አልፈዋል። ያ'ማ የሌላ ዘመን ነበር። ወንድማማችነት ላይ ነን።" ተራ ግንበኛ፡ ማንም ሰው፡ እንዲህ ማድረግ አያቅተውም። ያም ምንም አይደለም፡ ይህ ግን በኢየሱስ ክርስቶስ ያለውን አዲሱን ልደት፡ የነፍስ መዳን፡ ወይም እውነቱን በፍፁም ሊተካው አይችልም።

61 እንግዲህ፡ ይህቺ ኤልዛቤል። የአብርሃም ልጅ ነበረች፡ ልክ ነው፡ ጣዖት አምላኪ ልዕልት ነበረች። በዚያን ጊዜ ንጉሣዊ ቤተሰቧ፡ ንጉሣዊው ቤተሰብ፡ ለበኣሊም በነበራቸው ጨካኝ ታማኝነት ዝነኞች ነበሩ። አባቷ እ-ሰ-ታ-ሮ-ት ለሚባለው ጣዖት ካህን ነበር (ምን ብላችሁ እንደምትጠሩት፡ እኔ

አላውቅም ከታሪክ ያገኘሁት ነው)። አክዓብ እንደ ቆስጠንጢኖስ ያሉ ስልቶቹን ተጠቅመዋል። ይህም ከእስራኤል የሚዋሰን ታላቅ እና ኃያል ህዝብ ነበር፡ ስለዚህም...

62 ቆስጠንጢኖስ ትናንት ምሽት ምን አደረገ? ፖለቲከኛ እንጂ። የተለወጠ ሰው አልነበረም። ምን ለማድረግ ሞከረ? እንጸልይልሃለን ባሉት ጊዜ፡ ክርስቲያኖችን ተቀበላቸውና... (አስታውሱ፡ አሁን በዚያ ውስጥ፡ እየ-... እየተነጋገርንበት ያለነው ስለ ኒቆላውያን ነው)። እና እንዲህ አላቸው፡ እነርሱ ጸልየውለት ጦርነት ካሸነፈ፡ ክርስቲያን—እንደሚሆን ተናገራቸው። ጋሻዎቹን፡ በነጭ ቀለም፡ የመስቀል ምስል ስሎባቸው። ህልም አይቶ ነበር። የኮሎምበስ ሠራዊቶች የተወለዱት፡ ያኔ ነው፡ ጽናታቸው የሚወስዱበት ከዚያ ነው። ምንም አይነት የክርስቲያን ነገር ግን አላደረገም! ቅድስት ሶፊያ ተብሎ በሚጠራው የኒቆላውያን አብያተ ክርስቲያናት፡ በአንዱ ጉልላት ላይ፡ መስቀልን አስቅሏል። ትናንት ማታ እንዳልኩት፡ ለቤተክርስቲያን ያደረገላት የሚመስለው አንድ ነገር ያደረገው ያ ብቻ ነው፡ እኔ ከታሪክ ገጾች ያገላበጥኩትም ይሁን፡ ወይም ሌሎች የታሪክ ምሁራን የሚሉት ነገርም አንድ ነው። አሁን፡ ስለ መለወጡ የምናውቀው ነገር የለም። ግን ምን ወደ ማድረግ ገባ? ማድረግ የፈለገው ነገር፡ አሁንም፡ ሮምን በሙላት አይቷልና።

63 አሁንም ይህን እዩት፡ ስልቱን ተመልከቱት። በተጨማሪም በመጽሐፍ ቅዱስ፡ እግዚአብሔር፡ በመቶዎች እና በመቶዎች ዓመታት በፊት እንዴት እንደሚያረጋግጠው ተመልከቱ። እግዚአብሔር እዚህ ላይ፡ አክዓብ ይጠቀምበት የነበረውን ተመሳሳይ ስልት፡ ቆስጠንጢኖስም እንደተተቀመበት ይነግረናል።

64 እንግዲህ፡ ቆስጠንጢኖስ የሕዝቡ አብዛኛው ክፍል፡ ኒቆላውያን ክርስትያኖች መሆናቸውን አይቷል። አንዳንዶቹ "መናፍቃን" ይሏቸው ነበር፡ ጴንጤቆስጤዎቹን ነው፡ "መናፍቃን እና ሆሊ-ሮለሮች" ሌላ-ሌላም፡ ይባሉ ነበር። እውነተኛ ምልክቶች እና ድንቆች መገኛው ግን እርሱ ነው። **ስጋዊቷ** ቤተ ክርስቲያን ግን ድርጅት ወደመሆን እያደገች ነበር። ምን አደረገ? ቆስጠንጢኖስ ብልጣ ብልጥ ጨዋታ ተጫወተ። በዚህ በኩል አረማውያን ወዳጆቹ፡ በዚያ በኩልም ክርስትያን ወዳጆቹን ሰበሰበና፡ አብያተ ክርስቲያኖቹ አንድ ላይ ጉባኤ ጠራቸው፡ ወጥመድ ዘረጋ—እና... አረማዊነትን ወደ ክርስትና አስመጣ። ክርስትና እና አረማዊነት በጴርጋሞስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ተጋቡ።

65 እንግዲህ፡ ለዚህ ለዛሬ ማታ ያለው ነገር ምንድነው? አክዓብ ያደረገው ተመሳሳይ ነገር አደረገ። አክዓብ፡ መንግሥቱን ያጸና ዘንድ፡ ጣዖት አምላኪ ሴት፡ ኤልዛቤልን አገባ፡ ይህም መንግድቱን ለማጽናት፡ እና በእስራኤል ላይ ጥንካሬን ያመጣ ዘንድ ነው።

66 አሁንም አብያተ ክርስቲያናት እየሞከሩ ያሉት ይህ ነው። በሚቀጥለው ዓመት በ62 የሚለቀቀውን፡ መጽሐፍ ቅዱስ ከምን ለመስራት እንደሚሞክሩ አይታችኋል? መጽሐፉ አይሁዶችን የሚያስደስት፡ ካቶሊኮችን የሚያስደስት፡ እና ፕሮቴስታንቶችን የሚያስደስት መጽሐፍ ቅዱስ ነው። ኦህ፡ ወንድሜ! ከጋዜጣ ቆርጬ ሰቅዬዋለሁ። ዛሬ ማታም አላመጣሁትም፡ በቀደም ሙሉውን ሳነበው ሰምታችሁኛልና። ይኸው ነው፡ አያችሁ።

67 አቤት፡ ስለ ብልጽግና እነዚህ ነገሮች ይሞክራሉ! ስለ ብልጽግና እና ስለ ሰው ብዛት፡ የተቀደሱ የእግዚአብሔርን ነገሮች በየመንገዱ በተኗቸው። ቤተ ክርስቲያን ያደረገችው ይህንኑ ነው። በዚህም በእጃቸው በመጨባበጥ በሚል መርህ ብቻ አባላትን ማብዛት ተያያዙት፡ በዚህም ምክንያት፡ ያልተለወጡ ሰዎች እና ከሃዲዎች አበዙ። እውነተኛዋ የክርስቶስ አካል እንጂ፡ ድርጅት ወዳልሆነችው፡ ወደ መንፈሳዊቷ—ሰማያዊት የክርስቶስ አካል ግን፡ መግቢያ መንገዱ አንድ ብቻ ነው፡ ይህም በመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት በኩል ነው። ትክክል! ሐዋርያትን የነካቸው ያው ምልክትም፡ ቤተክርስትያኒቱም ነክቷታል። በትክክል እውነት ነው!

68 ስለዚህ፡ ማመቻመች የለብንም እንዲህ በማለት፡ "በቃ፡ ሄደን ከሴምብሊዮች ጋር ሕብረት እናደርጋለ። ከኦንሊ ጂሰስ ጋር ሕብረት እናደርጋለን። ከነ **እከሌ** ጋር፡ ወይም ከባብፕቲስት ጋር፡ ሜቶዲስት ጋር ሕብረት ለማድረግ እንሄዳለን።" ከእነዚህ ነገሮች ነፃ ሆነን! ከክርስቶስ ጋር ሕብረት እናድርግ። ምክንያቱም እነዚያ ድርጅቶች እያንዳንዳቸው ያው ናቸው፡ ይሁን እንጂ—የያዙት የራሳቸው ትምህርት እና አሸንክታቦች አሏቸው፡ እና ጉባኤ ማዘጋጀት ስትፈልጉ በአገሩ ላይ ፈቃድ እንዲሰጣችሁ ከሁሉ በፊት የበላይ ጠባቂውን ለማየት ትገደዳላችሁ። እንደ ትምህርታቸው ካላስተማራችሁ፡ ያባርሯችኋል፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ መጽናት አትችሉም። እግዚአብሔር ግን ይሄን አይታገስም፡ ይጠላዋል። ዳግመኛ-የተወለደ ክርስቲያንም እንዲሁ ነው። በዚያ ውስጥ ያሉ ብዙዎቹ ሰዎች በትክክል… ማገልገል የሚፈልጉ፡ ሕብረት ማድረግ፡ የሚፈልጉ ናቸው። ነገር ግን አይሆንላችሁም፡ ያባርሯችኋል። በቃ፡ ቢያባርሯችሁም፡ ቀጥሉ፡ መንፈስ ቅዱስ ብቻ ይኑራችሁ። ይህ በትክክል እውነት ነው። ነገር ግን፡ እያችሁ፡ እነርሱ—ዶግማውን ለማግኘት—ይመኛሉ። ብዙ ገንዘብ በምታገኙበት ስፍራ ላይ የእናንተ የሆነውን ማግኘት ይፈልጋሉ። ባፕቲስቶች በ44 ዓም መፈክር ነበራቸው፡ "ተጨማሪ አንድ ሚሊዮን በ44።" ምን አገኙ?

69 ታላቁ ወንጌላዊ ቢሊ ግራሃም፡ በሉዊስቪል በነበረ ጊዜ እንዲህ አለ፡ "እንዲት ከተማ ውስጥ ገብቼ… " አለ፡ "ቅዱስ ጳውሎስ ወደ አንዲት ከተማ ገብቶ፡ አንድ ሰው ያሳምናል፡ በሚቀጥለው ዓመት ሲመለስ—አንዱ ሰላሳ አፍርቶ ያገኘዋል፡ እሱ ካሳመነው አንድ ሰው፡ የልጅ-ልጅ-ልጅ-ልጅ-ልጅ-ልጆቹ ያያል።" እንዲህ አለ፦ "እኔ ወደ አንዲት ከተማ ሄጄ፡ ሰላሣ ሺ ሰዎችን እጠራለሁ፡ በሚቀጥለው አመት ስመለስ ግን ሰላሳ እንኳን አላገኝም።" ከተናገራቸው ነገሮች፡ ጥሩ ነጥብ—አስቀምጧል፡ ይሁን እንጂ ወንድማችን የተናገረው ትክክል ነው ማለቴ አይደለም። እንዲህ አለ፡ "እናንተ ሰነፍ ሰባኪዎች።" አለ፡ "እኔ ስማቸው እና አድራሻዎቻቸው እሰጣለሁ፡ እናንተ ግን ሄዳችሁ እንደመጠየቅ፡ እግራችሁ ጠረጴዛ ላይ ሰቅላችሁ ደብዳቤ ትጽፉላቸዋላችሁ።"

70 በዚህ ነገር—እጅግ አደንቀዋለሁ። ሰው እራሱን ሲመሰል፡ ግብዝ አለመሆኑ ደስ ይላል፡ በትክክል ቆማችሁ እራሳችሁን ሁኑ። እንዲህ አይነት ነገር ደስ ይለኛል። እኔ ግን እንዲህ እላለሁ፡ "ቢሊ፡ ጳውሎስ ያስመነውን ሰው የያዘው ማን ነበረ? ዋናው ነገሩ፡ ቢሊ፡ እጅ ወደሚጨባበጡበት እንዳይመለሱ ብታደርጋቸው፡ ተነስተው፡ 'አዎን፡ ኢየሱስን እንደ ግል አዳኜ

አድርጌ ተቀብያለሁ′ ብሎ በመሰከረበት ሰፍራ፡ እስኪሞት እና እስኪበሰብስ ድረስ ብታጸናው፡ በመንፈስ ቅዱስ ዳግመኛ በመወለዱ ምክንያት፡ ሌሎች አዳዲስ አማኞችን ያፈራል።″

71 ወንድሜ፡ አንተ ነህ ... በእሳት እያበበ ነው ያለው፡ አንተ ልታወጣው አትችልም። በኃይለኛ ነፋስ መካከል በእሳት እንደሚቃጠል ቤት ነው፡ አትችሉትም። ኧረ፡ ወንድሜ፡ የክርስቶስ አማኝ ነው፡ እረፍት የለውም፡ በየቦታው ያሰፋፋዋል። በቃ... በሰራ ላይ ነው። ኦህ፡ በጣም ደስ አለኝ! ኦህ፡ ማይ! ነፍስን እሳት በእሳት የሚያደርጋት የጥንቱ-ዓይነት ጥምቀት ነው! ዝም ብለህ መቆም አትችልም፡ ነፋሱ ይነፍሰብሃል፡ ፈጣኑ እና ኃይለኛው ነፋስ በአንተ ላይ መንፈሱ ይቀጥላል። እኔም እንጨት መወርወሬ የምቀጥለው፡ ወደ ፊት መቀጠል እንድትችሉ ነው። አዎን፡ ወዳጄ! የጳውሎስ አማኞች ማንም አይነቀንቃቸውም፡ ለራሳቸው ሞተው ለክርስቶስ መኖር እስኪችሉ ድረስ፡ ጳውሎስ ወደ ክርስቶስ እጅግ ያቀርባቸዋል፡ ሌላው ራሱ ይሰራዋልና። ትክክል ነው! እውነቱ ያ ነው።

72 የባፕቲስት ወንድሞቻችን ጥሩዎች ናቸው። ተጨማሪው አንድ ሚልዮን፡ ምን ይጠቅማሉ? አንድ ሚሊዮን ተጨማሪ ሰዎች ታፈራላችሁ እንጂ። እንግዲህ፡ ልታሰፍሯቸው ከፈለጋችሁ ቁጭ በሉና አንዳንዶቹን መዝግቧቸው። ችግር የለውም፡ ነገር ግን፡ ወንድሜ፡ እኛ የሚያስፈልጉን ሰዎቻቸው በበጉ የህይወት መጽሐፍ የተጻፈ፡ ከዓለም ፍጥረት ጀምሮ በታረደው፡ በደሙ ታጥበው፡ በመንፈስ ቅዱስ ተሞልተው፡ ተአምራትና ድንቅ የሚከተላቸውን ነው።

73 ታሪክ በሙሉ መርምሩ። ሁላችሁም የኒቂያን ጉባኤ አግኝታችሁ ብታነቡት ደስ ይለኛል፡ ሰማዕቶቹ ሁሉ የጴንጤቆስጤውን የእሳት ነበልባል እንዴት ይዘውት እንደነበር ያሳያችኋልና። ወንድሜ፡ አሁን እኔ እነግርሃለሁ፡ አንተ ባፕቲስት፡ ሜቶዲስት፡ እና ሌሎቻችሁም በሙሉ ሆይ፡ አሁን፡ ይህ የጴንጤቆስጤ ድርጅት... እውነተኛው ብርሃን እሱ አይደለም፡ እውነተኛው ብርሃን ግን፡ የጴንጤቆስጤ ልምምድ ነው። በዚህ ሁሉ... እነዚህን ታሪኮች በሙሉ፡ ቆፍሬ ለማውጣት፡ አሁን ከቀናት ወደ ቀናት ፈጅቶብኛል፡ ከጴንጤቆስጤ ቀን ጀምሮ እስከዚህ ጊዜ ድረስ በሕይወት ሕያው ሆኖ የኖረው የጴንጤቆስጤ ነበልባል ብቻ ነው። አዎን፡ ወዳጄ! ገፍተውታል።

74 አንዳንዶቹ እንዲህ ይላሉ፡ “ታላቋ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ማዕበሉን ተቋቁማ፡ ጸንታለች። ይህም፡ ቤተክርስትያኒቱ እውነተኛ መሆኗ ያረጋግጣል።” እንዴ፡ ይህ ለእኔ እንግዳ ነገር አይደለም፡ መንግስት እና ሌላው ሁሉ ከበስተጀርባዋ ቆመውላት′ማ፡ በደንብ መኖር ትችላለች። ነገር ግን—እጅግ የሚያስደንቀው፡ ይህች ስትጎተት የኖረችው፡ ታናሺቱ መንጋ፡ ስትሰደድ፡ ወደ እስር ስትወረወር፡ በመጋዝ ስትሰነጠቅ ኖራለች። እንዴት ብለው ተወጡት? የሕያው እግዚአብሔር መንፈስ በሕያው በሰውነታቸው ስለሚኖር። የገሃነም አጋንንት በሙሉ አያሸንፏቸውም! “በዚህች ዓለት ላይ ቤተ ክርስቲያኔን እሠራለሁ፡ የገሃነም ደጆችም አያሸንፏትም።” እውነተኛው ነገር ይህ ነው። ለእነዚህ የሜቶዲስቶች፡ እና የሌሎች ሰባኪዎች ሁሉ፡ መንፈስ ቅዱስን የሚሰጠው ያ ነው። እያችሁ፡ ተነስተው፡ አንዳች ነገር እንዲያደርጉላችሁ ያስችላቸዋል። በፍጹም አይወድቅም።

75 ያን፡ ግብዝ አክዓብ። እያችሁ፡ ወጣና፡ እንዲህ አለ፡ “አሁን፡ ሁሉንም በአንድ ላይ አድርጌ፡ ይህችን ታላቅ አገር ከሰራኋት። ያቺ የዚያ ሰው ሴት ልጁ ካገባኋት፡ ያኔ፡ ከ... ከእርሱ ጋ—ወዳጀሞች እንሆናለን።” ምን እያደረገ ነበር? ብኩርናውን እየሸጠ ነበር።

76 ስለዚህ፡ የፕሮቴስታንት ቤተ ክርስቲያን እንደገና ሕብረት ለማድረግ ከካቶሊክ ጋር ወደመሆን **ስትመለስ**፡ ያኔ ያደረገችውን ተመሳሳይ ነገር ታደርጋለች። አክዓብ የኖረበት ዘመን...

77 ሶስት ጊዜ አልፏል። በእኩለ ሌሊት በእስራኤል የጉዞ ልምምድ ነበረ፡ ዛሬም እንደገና **ወደዚህ** ወደ እኩለ ሌሊት ደርሰናል፡ እንደገና **ወደዚህ** ወደ እኩለ ሌሊት መጥተናል። ከዚህ በፊት ሦስት ትውልዶች፡ **ወደዚህ፡ ወደዚህ፡** እና **ወደዚህ** ገቡ።

78 እንግዲህ፡ እዚግ ጋር ካስተዋላችሁ፡ አክዓብ ህዝቡን ለማጠናከር ኤልዛቤልን አገባ። ቆስጠንጢኖስ ያደረገውም ያው ነው። ትታላቅ ቤተ ክርስቲያን ሰራ፡ ከእምነበረድ የተሰራ መሰውያ ሰራበት፡ አንዱን ሰው፡ ጳጳሱን በደንብ አለበሰው፡ በዚያም አኖረው። ይህም ለእነርሱ ሕያው አምላካቸው ነበረ፡ የሚያናግራቸው፡ ስለ—ኃጢአቶቻቸው የሚነግራቸው፡ የማትረባ ለብ ያለች ቤተ ክርቲያን በዚህ ደስተኛ ሆነች፡ በዚያም ጠፉ። አዎን! ያ ነው! ይሁን እንጂ፡ ዳግም የተወለደ ሰው ግን በዚህ ደስ አይለውም፡ ያን ነገር ከተቀበሉ በኋላ የአረማውያን የጸሎት ስርዓት የተሞሉ በዓላት አስተዋወቁ። ምን አደረጉ? ጁፒተርን አውርደ፡ ጴጥሮስን ከፍ አደረጉ። ቬነስን አውርደው፡ ማርያምን ከፍ አደረጓት። ይህም ወደ ክርስትናው ስልጣን አረማዊነትን አስ—አስመጣ።

79 አክዓብም ኤልዛቤልን ባገባ ጊዜ፡ እንዲሁ አደረገ። ጣዖት አምልኮን ወደ እስራኤል አመጣ። ኤልዛቤልስ ምን አደረገች? እጇን ማግኘት የምትችለውን ነብይ ሁሉ ገደለች። ልክ ነው? ጳጳሶቹም እንዲሁ አደረጉ። እጃቸው የምታገኘው ክርስትያን ሁሉ፡ ገደሉት።

80 በዚያ ዘመን ግን የጥንቱ ኤልያስ፡ ኮከባቸው ነበረ! ኦህ፡ አዎን፡ ወዳጄ! ሲናገራቸው፡ አይፈራም ነበር። አዎን፡ ወዳጄ! **የዘመኑ** ከኮብ እሱ ነበር። አንድ ጊዜ “ጌታ ሆይ፡ ብቻዬን ቀረሁ፡” እስከማለት ደርሶ ነበረ።

81 እግዚአብሔር ግን፡ “ኤልያስ ሆይ፡ ቆይ፡ ቆይ፡ ቆይ አንዴ፡” አለው። ኧህ-ህህ። “የደበቅኳቸው ሰባት መቶ፡ በዙርያ አሉ። አየህ? የት እንዳሉ አንተ አታውቅም። እዚያው፡ በፈሪሳውያን፡ በሰዱቃውያን፡ በባፕቲስት፡ ሜቶዲስት፡ እና በፕሪስባይተሪያኖች ዘንድ አሉ፡ ጠብቀን ብቻ፡ ከዚያም—አወጣችኋለሁ። አየህ? በዚያ ውስጥ አሉኝ። እና... እነርሱም የ—የ—የኔ ናቸው፡ ለበአሊምም ጉልበታቸውን አላንበረከኩም።” ጥንታዊው ኤልያስ ግን ለዚያ ዘመን የእግዚአብሔር ድምጽ ነበረ። በክርስቶስ የመጀመሪያ ምጽዓት ወቅት የእግዚአብሔር ድምፅ ምሳሌ ነበር፡ አሁንም በቅዱሳት መጻሕፍት መሠረት፡ በክርስቶስ ዳግም ምጽአት ውስጥ የሚመጣ ድምጽ ምልክት ይሆናል።

82 እና፡ ይህች ኤልዛቤል፡ ወደዚያ በመጣች ጊዜ፡ የእግዚአብሔርን መሠዊያዎች ሁሉ ቆርጣ የራሷን መሠዊያዎች ለማቆም አሰበች። በጣዖት ፊት የሚሰግዱ እስራኤላውያንም ነበሯት። ቆስጠንጢኖስም የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያንን ለመስራት ያደረገው ስራ ያ ነው። ወደ—ክርስትናው ቤተ

ክርስቲያንአረማዊነትን አመጣ፡ በጣዖት ፊት የሚሰግዱ ክርስትያኖችም ነበሩት። ያ እንደገና የጨለማው ዘመን ነው፡ የእስራኤል የጨለማ ዘመን፡ በጣዖታት ፊት መስገድ፡ ለ—ለቤተ ክርስቲያን የጨለማ ዘመን ነው። ኤልያስም በዘመኑ ኮከብ ነበር።

83 እስራኤል ለበአለም እንድሰግዱ አደረገቻቸው፡ ካቶሊክም በትያጥሮን ቤተ ክርቲያን እንዲሁ አደረገች።

84 አሁን፡ እዚህ ሌላ የሚያስደንቅ ነገር እንድታስተውሉ እፈልጋለሁ፡ ይህ ታሪኬን እያዘጋጀሁ ነበርኩና። እራሷን ነቢይት ነኝ... የምትለውን ብሏታል ኢየሱስ። "ራሷን ነቢይት ነኝ፡ (የምትለው) ያቺን ሴት ኤልዛቤል።" አሁን፡ ተመልከቱ፡ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ህዝቡ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲያነብ አትፈቅድም ምክንያቱም ቃሉን በመለኮት የሚያቀርበው ካህኑ ብቻ ነው ይላሉ።

85 እንግዲህ፡ የነቢይ ትክክለኛ ትርጓሜ ይህ ነው። ነቢይ የእግዚአብሔር ቃል መለኮታዊ ትርጓሜ አለው። በትክክል እውነት ነው። አንድን ግለሰብ፡ "ነብይ ነው" ካሉት፡ እንዴት "የተሳሳተ መገለጥ፡" ያለው ነው ሊሉት ይችላሉ? እዚህ ጋርም ዘላለማዊ ልጅነት እንደሚሉት ይመስላል። አይታችኋል። አያችሁ? ነገሩን—ነገሩን፡አይታችኋል... **ነብይ** ማለት "የጌታ ቃል የሚመጣለት፡ መገለጥ የሚመጣለት፡ እውነተኛ ገላጭ ማለት ነው።" **ነቢይ** የሚለው ቃል ትርጉሙ "የመለኮታዊ ቃል ገላጭ" ማለት ነው። ኢየሱስም አላቸው፡ "ከእናንተ መንፈሳዊ ወይም ነቢይ የሆነ ሰው ቢኖር፡ እኔ ጌታ እግዚአብሔር እናገረዋለሁ። የሚናገረውም ከተፈጸመ፡ እርሱን ሰሙት፡ እኔ ከእርሱ ጋር ነኝ። ይህ ካልሆነ ግን፡ እሱን አትስሙት።" ይኼው ነው። መለኮታዊው—የእግዚአብሔር ቃል፡ የጌታ ቃል ወደ ነቢያት ይመጣ ነበር።

86 አሁን ግን፡ ያኔ ያቺ **ቤተ ክርስቲያን** "ነብይ" ናት አሏት። አስተውሉ አሁን፡ ከዚህ ከኒቆላውያን፡ አሁን ወደ "**እሷ**" ተቀይሯል። አሁንስ እያችሁትን? "ኤልዛቤል" ናት። ትናንት ማታ፡ "የበልዓም ትምህርት" ነበረ። እያችሁ፡ "የኒቆላውያን ትምህርት" እና "የበልዓም ትምህርት።"

87 ያኔ፡ ከእስራኤል ጋር ያመነዘረ በልዓም ነበር። ኒቆላውያንስ ያደረጉት ምን—ምን—ምንድነው? ተቋም ሰሩ። እነዚህ ሁለቱ አንድ ላይ አድርጋችሁ **እሷን** ታገኛላችሁ፡ "ቤተ ክርስትያን።" አዎን! ራእይ 17፡ "በብዙ ውኆች ላይ የምትቀመጥ ታላቂቱ ጋለሞታ።" ሴተኛ አዳሪ፡ ሴት። በምን፡ እና እንዴት ሴተኛ አዳሪ ሆነች? ዝሙትን፡ መንፈሳዊ ዝሙትን ትፈጽማለች፡ ቃሉን ለሰዎች በተሳሳተ መንገድ ትተረጉማለች። ከአክራሪነትዋ ራቁ! እውነተኛ አክራሪነት ይህ ነው። ትክክል።

88 አሁንም፡ እነሆ፡ ስለ ራሷ ነቢይት ነኝ፡ "ዋናዎች እኛ ነን! ዋናው ጉባኤ እኛ ነን! አሁንም እንደገና የሎዶቅያ ጉባኤ፡ የሰዎቹ ጉባኤ እኛ ነን፡ **እንዲህ** እና **እንዲህ፡** እና **እንዲህ፡** ይሁን ብለን አጽድቀናል። እኛን ስሙ!'' ግን...

89 ስለ ፍሬዘር ልጅ ስለ ኤልሳቤጥ ፍሬዘር ሊጠይቀን፡ እዚህ የሚኖር—ቄስ ወደ እኔ መጣ። እና "ብጹዕነታቸው—ወይም ቢሾፑ... የፍሬዘርን ልጅ፡ አጥምቀሃት እንደሆነ ሊያውቁ ይወዳሉ" አለኝ። "ካቶሊክ ሆናለችና፡" አለኝ።

"አዎን፡ አውቄአለሁ፡" አልኩት።

“አጥ—አጥምቀሃታል ወይ? ” አለኝ፡

“አዎን፡ ወዳጄ፡” አልኩት።

“እንዴት ነበር ያጠመቅካት? ” አለኝ፡

“በክርስትያናዊ ጥምቀት፡” አልኩት። ኧሀ-ሀሀ።

አለኛም፡ “ምን ማለትህ እንደሆነ፡ አልገባኝም? ”

እንዲህ አልኩት፡ “ክርስቲያናዊ ጥምቀት፡ የመጽሐፍ ቅዱስ ብቸኛው መንገድ ነው። በክርስትና ጥምቀት ለመጠመቅ አንድ መንገድ ብቻ አለ። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያለ እያንዳንዱ ሰው የተጠመቀበት መንገድ ‘በኢየሱስ ክርስቶስ ሰም’ በጥልቅ ውኃ ውስጥ በመጥለቅ ነው።”

90 ማስታወሻውን ጻፈ፡ እንዲህ እየጻፈ ተናገረ። “የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ይህን ታደርግ እንደነበር፡ ታውቃለህ አይደል፡” አለኝ።

“መቼ? ” አልኩት፡ እና፡ “ከለንደን እና ከሌሎች ከየትኛውም ቦታ ማግኘት የምችላቸው ጥንታዊ ታሪኮች ሁሉ ይዣለሁ፡” አልኩት። ይህም ሰዓቲቱ ቀርባ የሆነ ነገር ሊሆን ሲል፡ እኔም ይህን ማጥናት እንድችል ይረዳኛል። እምም። አልኩትና፡ “የት ነው—እኔም ማወቅ እፈልጋለሁ።” ሄጄም...

አለኛም፡ “በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ፡” “ነዋ፡” አለኝ።

“ምን አልክ አባክህ... ? ” አልኩት፡

“የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያንን ያደራጀት’ኮ ኢየሱስ ራሱ ነው፡” አለኝ።

“ታዲያ፡ ጴጥሮስ የመጀመሪያው ጳጳስ ነበረ ወይ? ” አልኩት፡

“በጣም በእርግጠኛነት፡” አለኝ።

እንዲህ አልኩት፡ “እኔ፡ኮ ‘ቤተክርስትያኒቱ የማትለዋወጥ ናት ብዬ አስብ ነበር፡ እንዳይለወጥም ቅዳሴ ሁሉ በላቲንኛ የሚደረገው ይመስለኝ ነበር።’”

“ያ’ማ እውነት ነው፡” አለኝ።

91 እኔም “ታዲያ፡ እናንተ ግን ከጊዜ በኋላ ለውጦች አድርጋችኋል፡” አልኩት። “ያን መጽሐፍ ቅዱስ የካቶሊክ መጽሐፍ ከሆነ፡ እንግዲያውስ እኔም የጥንቱ-ካቶሊክ ነኛ፡” አልኩት። አያችሁ? በትክክል። “እንግዲያውስ፡ እኔም የጥንቱ-ካቶሊክ ነኝ፡” አልኩት። አክዬም እንዲህ አልኩት፡ “በርግጥም ለውጥ አድርጋችኋል... ”

እሱም “አየህ፡ አሁን፡ ምን መሰለህ፡ መጽሐፍ ቅዱስ’ኮ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ነው፡” አለኝ። “እግዚአብሔር’ኮ በቤተክርስቲያኒቱ ውስጥ ነው፡” አለኝ።

እኔም “እግዚአብሔር’ማ በቃሉ ውስጥ ነው፡” አልኩት። በትክክል።

92 “የሰው ሁሉ ቃል ውሸት ይሁን፡ ቃሌ ብቻ እውነት ይሁን።” ኢየሱስ ራሱ የጻፋፈው ብቸኛ መጽሐፍ (አሁንም እላችኋለሁ።) ይህ የራእይ መጽሐፍ ብቻ ነው። እሱ ያደረገው የመጀመርያው ነገር አምላክነቱን መግለጥ ነው፡ ይህን በሙላት ገልጦታል። እንዲህም አለ፡ “ከውሰጡ አንዳች የሚቀንስ ወይም የሚጨምር ማንም ቢኖር፡ እርሱም (ድርሻውን) ከሕይወት መጽሐፍ ውስጥ ይወሰድበታል። የሚያነበው፡ ወይም የሚሰማው ብጹዕ ነው። በእርሱ

ላይ አንዳች ነገር የሚጨምር ወይም የሚቀንስ ርጉም ነው።" አደጋው ይሄውና፡ ተመልከቱት። ስለዚህ በጭራሽ አትጨምሩበት፡ ባለበት ተዉት፡ እና መንገዳችሁን ቀጥሉ።

93 ጠይቁት፡ ትሑታን ከሆናችሁ መንፈሱ ይገልጥላችኋል። አያችሁ? በትክክል። አሁን፡ ስለዚህ ውስብስብ አይደለም። እግዚአብሔር... ኢየሱስ አብን አመሰገነ... እንዲህ በማለት፡ "አባት ሆይ፡ እነዚህን ነገሮች ከሊቃውንት ከቢሾፖች እና ከካርዲናሎች እንዲሁም ከጠቅላይ አለቆች፡ ዓይን ሰውረህ፡ መማር ለሚወዱ፡ እንዲሁም ለሕጻናት፡ ስለገለጥክላቸው፡ አቤቱ— አመሰግንሃለሁ።" አያችሁ?

94 የሚያስፈልጋችሁ ያ ነው። "ሰዎች ማን እንደሆንኩ ይላሉ? " ብሎ በጠየቃቸው ጊዜ እንደመጣው ብቻ የሚመጣ የእግዚአብሔር መገለጥ ነው፡

እርሱም "አንተ ክርስቶስ፡ የሕያው የእግዚአብሔር ልጅ ነህ፡" አለው።

95 እርሱም አለው፡ "ስምዖን ሆይ፡ ይህ ከትምህርት ቤት አልተማርከውም። አየህ? ማንም አልነገረህም። የመጣው፡ ከሰማይ የወረደ መገለጥ ነበር። በዚህች ዓለት ላይ ቤተክርስቲያኔን እገነባለሁ፡ የገሃነም ደጆችም ሊያሸንፏት አይችሉም።"

96 አቤል በመጀመሪያ ላይ ያገኘው መገለጥ ያ ነው። በመገለጥ ነው፡ ድሮም በመገለጥ፡ ዘንድሮም በመገለጥ፡ ወደፊትም እንዲሁ ይቀጥላል። በትክክል።

97 እንግዲህ፡ አሁን ከዚህ ሴት እንደነበረች ተገንዝበናል፡ እና **ሴት** "የቤተ ክርስቲያን" ምሳሌ ናት። (ልክ ነው? ክርስቶስ የሚመጣው ለማን ነው? ለሙሽራይቱ፡ ንጽሕት፡ ድንግል ለሆነች ሴት።) እቺ አሮጌት ሴት ግን፡ ራሷን የእግዚአብሔር ቤተክርስቲያን እኔ ነኝ ትላለች፡ ነገር ግን፡ ምን ነበረች፡ በሀብትና በዕንቁ፡ በሁሉም ነገር ያጌጠች፡ የዝሙትዋም ርኩሰት ጽዋ ይዛ፡ የምድርን ነገሥታት ሁሉ በወይን ጠጇ አሰከረቻቸው። ልክ ነው?

98 እና፡ እዚህ ጋር "ኤልዛቤል" ተብላ እንደምትታወቅ አይተናል። ኤልዛቤልም፡ ልክ በእስራኤል ልጆች መካከል እንደገባች፡ ኤልዛቤል ያደረገችው ክፋት፡ እነሱን ሁሉ ገድላ የምትችለውን ሁሉ አደረገች፡ እና— መሠዊያዎቿንም ሠራች። ልክ ነው? የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ያደረገችውም ያው ነው። በትክክል ያ ነው። አሁን ግን ትንሽ ዘለቅ ብለን እናንብብ። ይህም እጅግ ያሰገርማችኋል። አንዳንዴ በደንብ ትመገባላችሁ፡ ያን ጊዜ ትደነቃላችሁ።

> ... **ራሷን ነቢይት ነኝ ብላ** ጠራች፡ (እንግዲህ፡ ይህ ማለትዋ፡ "የቃሉ ተርጓሚ እኔ ብቻ ነኝ" ማለትዋ ነው።) **ባሪያዎቼንም** እንዲሴስኑ፡... **ለጣዖት የታረደውም እንዲበሉ** ታስተምራለች።

99 "በኤደን ገነት ስለነበረ ፍሬ ስለ መበላት" "የእባቡ ዘር፡" በተመለከተ አንድ ወንድም ጥያቄ ጠይቆ ነበር። እዚህጋ "መብላት፡" ሲል፡ (ገብቷችኋል አይደል? ) ምን እንደሆነ አይታችኋል። አያችሁ፡ ነገሩ፡ መንፈሳዊ ነገር ነው። እና... በተጨማሪ...

> ስለ**ዝሙትዋም ንስሐ እንድትገባ ጊዜ ሰጠኋት— ስለዝሙትዋ ንስሐ እንድትገባ ግን፡ አልወደደችም።**

**እነሆ። አልጋ ላይ እጥላታለሁ፡** (ምን አይነት አልጋ? የዓለማዊነት አልጋ። ዛሬ እሷ ያለችበት ሁኔታ ያው ነው።) **ከእርሰዋም ጋር የሚያመነዝሩትም ከሥራቸው ንሰሐ ባይገቡ፡** ወደ **ታላቅ መከራ እጥላቸዋለሁ።** (ያም ታላቁ መከራ ማለት ነው።)

**ልጆቿ... ንም በሞት እገድላቸዋለሁ፡...**

100 ዋ! ምኖቿ? ይህች አሮጌት ለካ ልጆች ነበሯት። አሁን ራዕይ 17። እስኪ ትናንት ማታ... ? ሁላችሁ እዚህ እንደነበራችሁ አሰባለሁ። በጣም ጥሩ። ራዕይ 17፡ ይህች አሮጌቷ ሴተኛ አዳሪ፡ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን፡ "ጋለሞታ" "የጋለሞታዎች እናት፡" በመባል ትታወቃለች። **አብያተ ክርስቲያናት** ናቸውና፡ ወንዶች ሊሆኑ አይችሉም።

101 አሁን የሉተራን ቤተክርስትያንን ጨምሮ፡ እነዚህ ሁሉ ከየት የመጡ ናቸው? እነዚህ ሁሉ ድርጅቶች ከወዴት መጡ? መጀመሪያቸው የት ነው፡ ሎዶቅያ? ወደ እንደዚህ አይነት ነገር ያደጉት ኒቆላውያኖቹ ናቸው፡ እንደገና ተመሳሳይ ነገር እየሆነ ነው። ወንድሜ፡ አንተ ምንም ማድረግ አይቻልህም። እነሆ፡ ኤልያስ በዘመኑ ተቃውሞታል። ዮሐንስም በዘመኑ ተቃወመው። አዎን፡ ወዳጄ! በልባችሁም እንዲህ አትናገሩ፡ "አብራሃም አባት አለን አትበሉ፡ ከእነዚህ ድንጋዮች ለአብርሃም ልጆች ያስነሣለት ዘንድ እግዚአብሔር ይችላልና።" አያችሁ? ምንም ማድረግ አትችሉም።

102 ስለዚህ፡ ልጆች ነበሯት። እውነተኛዋ ኤልዛቤል ልጆች ነበሯትን? አዎን፡ ነበሯት! ተከታተሉ፡

**... ልጆቿን እገድላ**ለሁ...

103 ምንድን? የካቶሊክ ቤተክርስቲያን ልጆች፡ የፕሮቴስታንት የሐይማኖት ተቋማት ናቸው። አያችሁ። እውነት'ኮ ነው፡ እነርሱም ተመሳሳይ ነገር እየሰሩ ይገኛሉና። መጽሐፍ ቅዱሳዊ ባልሆነ፡ በተሳሳተ አጠማመቅ እየተጠመቁ እና ስለ መንፈስ ቅዱስም እጆችን እያንቀጠቀጡ፡ ወደ ውስጧ ይጠመቃሉ፡ "በኢየሱስ ክርስቶስ" በማለት ፈንታ "በአባት፡ ልጅ፡ መንፈስ ቅዱስ" ይላሉ። መጽሐፍ ቅዱስ ጋር የሚቃረን ነገር ሁሉ ማድረግ ብቻ ናቸው። አሁንም! እንዲሁ እየተጓዙበት ይገኛሉ።

104 የእሷም ሴት ልጅዋ ጎቶልያ ትባላለች፡ ጎ-ቶ-ል-ያ። ይህችም... ኤልዛቤል፡ ማን ናት፡ ጎቶልያም የይሁዳ ንጉስ ልጅ ከነበረው፡ ከኢዮራም ጋር ተጋባች፡ ወዲያውም የበአሊም መሰዊያዎችን በኢየሩሳሌም ማቆም ጀመሩ። እንግዲህ፡ ይሄን ለማወቅ ወደ ታሪክ መሄድ አይጠበቅባችሁም፡ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አለ። አያችሁ? ልጇ፡ ጎቶልያ፡ ኢዮራም የተባለውን የኢዮሳፍጥ ልጅን፡ አገባች። ሴቶች ልጆቿም እሷ እንዳደረገች እንዲሁ አደረጉ።

105 ኦህ፡ ማይ! አይታያችሁም ወይ? ወንድሞች ሆይ፡ እነኚህ ድርጅቶች ሁሉ እንዴት እንዳደረጉ አያችሁን? በሉተር እና በሌሎች በኩል፡ ስተት ብለው ገቡና፡ መንፈስ ቅዱስን እንዲሰራ ከመፍቀድ ይልቅ እራሳቸውን አደራጁ። ጴንጤቆስጤም እንዲሁ ተመሳሳይ ነገር ፈጸመች። መንፈስ ቅዱስን በራሱ መንገድ ስራውን እንዲሰራ እንዲቀጥልም፡ አልፈቀዱለትም፡ የመጣ ብርሃን

ሁሉ፡ በቃሉ መርምራችሁ፡ ቀጥሉ። እነርሱ ግን መደራጀት ስለፈለጉ፡ መንፈስ ቅዱስ መሪ እንዲሆን አልፈቀዱለትም እና በፊታቸው ከሚያመጣላቸው ነገር ሁሉ ተለያዩ። እንደገና ወደ ኋላቸው በመመልስ ከዚያ ነገር ጋር ተጋቡ! በትክክል። ወደዚያ ዘመን ሰንደርስ፡ በዚያ በመንገድ ላይ የሚጠብቃችሁ ምን እንደሆነ ተመልክቱት። አያችሁ? እንደገና ወደ ኋላ ጋብቻ ፈጸሙ! ኢየሱስም እዚህ ሲናገር፡ "ይህች... ኤልዛቤል፡ እራሷን 'ነቢይት' ነኝ የምትለውን፡ በዓለማዊነት አልጋ ላይ እጥላታለሁ፡ ልጆቿንም እገድላቸዋለሁ" (በምን፡ አለ... ? ) "በሞት።"

106 ይህ... ልጆቿ የሚሞቱበት ሞት ምን አይነት ሞት ነው? እሰኪ እዩአችቸው አሁንም ሞተዋል! የመንፈስ ሙታን! መገለጥ የላቸውም! ድርጅታቸውን ያውቃሉ፡ ካቴኪዝምን ያውቃሉ፡ ስለ ቤተ ክርስቲያን አስተምህሮአቸውን ያውቃሉ፡ እግዚአብሔርን ስለ ማወቅ ብትሉ ግን፡ አንዳንዶቹ ሆቶንቶቶች ስለ ግብጽ ሰራዊት የሚያውቁትን ያህል እንኳ ምንም አያውቁም፡ ስለ መንፈስ ቅዱስ ማወቅ ከተባለ፡ እውነቱ ይህ ነው። ቅብዝብዞች፡ የእግዚአብሔር መንፈስን "ሟርት፡" ወይም "ሰይጣን" ነው... ለማለት ይዳዳቸዋል፡ ይህም... መናፍስት የመለየት፡ አጋንንትን የመገሰጽ፡ እና የመሳሰሉ ጸጋዎችን በማየታቸው ነው። "እንዴ፡ እሱ'ኮ የድርጅታችን አባል አይደለም። የእነኚህ ጎራ ነው፡ ኡህ፡ **ብርርር**።" አያችሁ፡ በቃ ምንም አያውቁም። ከዚያ ሰ—ሰም ያውጡላቸዋል "ኦንሊ ጂሰስ፡" ወይም "ሆሊ-ሮለር" በማለት ሰያሜ ይለጥፋሉ፡ ወይም—ወይም እንደዚህ የመሳሰሉ ነገሮች ይሰይማሉ። በቃ አያውቁትም!

107 ያ ነገር የሚጋለጥበት ጊዜ ቅርብ ነው። በትክክል። እኔ ከዚህ ፑልቢት ጀርባ መቆሜ እርግጠኛ እንደሆነ ሁሉ እግዚአብሔር በእርግጠኝነት ይህን ያደርጋል፡ እኔ እዚህ መቆሜ እውን እንደሆነ ሁሉ ልጆቹን በርግጥ ያወጣቸዋል። የሰማይ አምላክ ይህን ያውቃል። የጌታ ነብይ እንደሆንኩ፡ የጌታ ባርያ እንደሆንኩስ ታምናላችሁን፡ እንግዲያውስ ሰሙኝ። እንግዲህ በደጅ ቀርባለች። አዎን፡ ወዳጄ።

108 "ልጆቿ በመንፈሳዊ ሞት ይገደላሉ።" አሁንም ተመልከቷቸው፡ ተራ እና ቀዝቃዞች ናቸው። ይህን ግን... የእኛን ግን ተመልከቱ... ስለ ባፕቲስቶች እና ፕሪስባይቴሪያን ማውራት አይጠበቅብንም፡ ለብዙ አመታት እንደሞቱ እናውቃለንና። ምንድን...

109 ሉተር፡ የጽድቅ ሪቫይቫል እንደጀመረ፡ በዚያው ቢያስቀጥለው... እንዲሁ ቢቀጥል ኖሮ፡ ይህ—ይህ የአሁን የጴንጤቆስጤ ታላቅ ንቅናቄ የሉተራን ቤተ ክርስቲያን ይሆን ነበር። ያ ብርሃን ዌስሊ በተከተለው መንገድ፡ በቅድስና በኩል በመጣ ነበር። ሉተር... ይህን መከተል አልቻለም። አልቻለም፡ ወዳጄ፡ ቀድሞውኑ ሉተራኖች ናቸው።

110 ከዚያም ዌስሊ መጣ። ዌስሊ ከሞተ በኋላስ፡ ምን ተፈጠረ? ያንን አደራጅተው፡ ዌስሊያውያን ሜቶዲስት፡ ፕሪሚቲቭ ዌስሊ-... አቤት፡ ሁሉም አይነቶች ሜቶዲስታዊነት ሰሩ። አያችሁ? ታላቅ ሪቫይቫል ነበራቸው... እራሳቸውን፡ ወደ ማደራጀት ከጣሉ በኋላ ግን፡ በጴንጤቆስጤ በልሳኖች እየተናገሩ የጸጋ ሰጦታዎችን ወደ ማቃናት ባደረሱት ጊዜስ? ዲያብሎሶች ናቸው አሏቸው እንጂ፡ ኮሸ አላላቸውም።

111 አሁንስ ጴንጤዎች ምን አደረጉ? እነሱ ያደረጉት ተመሳሳይ ነገር አደረጉ! አሁንስ በምን አይነት ሁኔታ ውስጥ ይገኛሉ? ያለ ጥርጥር ጨርሰው የሞቱ ናቸው። አዎን፡ ወዳጄ! በትክክል። "ልጆቿን አልጋ ላይ—በሞት አልጋ ላይ እጥላቸዋለሁ፡ እገድላቸውማለሁ።" እሺ እንግዲህ፡ እናንተም እንድታዩት እስኪ—ላንብበው፡ 22ኛው ቁጥር ይመስለኛል።

> እነሆ **በአልጋ ላይ እጥላታለሁ፡ ከእርሰዋም ጋር የሚያመነዝሩትን** በታላቅ **መከራ እጥላቸዋለሁ፡** (በ—በታላቁ መከራ)...

112 እየሆነ ያለው ያ ነው። አሁን እዚህ ጋር እንዴ ላቁመው፡ አስታውሱ፡ እነዚያ ወደ ታላቁ መከራ—ወደዚያ ውስጥ የሚወረወሩ ሰዎች፡ በመብራታቸው ውስጥ ዘይት ያልነበራቸው ተኝተው የነበሩ ደናግል፡ የአንድ ድርጅት አባላት፡ መልካም ሰዎች፡ ወደ ቤተ ክርስቲያን ሄያጆች፡ ወዘተረፈ የነበሩ፡ በኋላ ግን ዘይትን ፍለጋ ወጥተው፡ የረፈደባቸው ሰዎች ናቸው። አያችሁ፡ ወደ ታላቅ መከራ እጥላታለሁ፡ ወደዚያ ትገባለች፡ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ትገባበታለች፡ ልጆቿም በሙሉ ከእሷ ጋር፡ ወደ ታላቁ መከራ ይገባሉ።

> **... ከሥራዋ ንስሐ ባይገቡ።**

113 ቤተክርስቲያኒቱ ራሷ፡ እና ልጆቿም ደግሞ (ማለት ድርጅቶች እንጂ)፡ በውስጧ ያሉትን ልጆች—አይደለም፡ እንደ ምስኪን ካቶሊኮች፡ ባፕቲስቶች፡ ፕሪስባይቴሪያን፡ ወይም ጴንጤቆስጤዎች፡ በዚያ ውስጥ ያሉትን ሰዎች አይደለም። ለእነርሱ እጅግ አዝንላቸዋለሁ። በቃ፡ "አንተ፡ እ... "

"ክርስቲያን ነህ? "

"እኔ፡ ፕሪስባይቴሪያን ነኝ።" ኡህ!

114 "በፈረስ ግልቢያ አሳማ እስከነ ኮርቻዋ ነበረች" ከማለት ያልተናነሰ አባባል ነው። ስለዚህ ምን ማድረግ ይቻላችኋል? በቃ፡ ፋይዳ ቢስ። ለመቀለድ መፈለጌ አይደለም፡ ይህ... ይህም ወንጌል ነውና... ለቀልድ ስፍራ የለንም፡ ያ—ያም አይገባምና። አያችሁ? ምሳሌ ለመስጠት ፈልጌ ነው። አያችሁ? ያ ግን—ትክክል ነው። አያችሁ፡ ፋይዳ ቢስ ከመሆን የዘለለ—አንዳች አይጠቀሙበትም።

"እኔ ጴንጤ ነኝ።"

115 ፋይዳ ቢስ ከመሆን የዘለለ አንዳች አይጠቀሙበትም። አሰራ አንድ ጊዜ-አርባ የድርጅታቸው አባል ልትሆን ትችላለህ፡ ቁምነገሩ ግን ዳግም-የተወለደ የእግዚአብሔር ልጅ ነህ ወይ? በእውነቱ፡ ሰውን ሁሉ ከልብህ፡ ከነፍስህ ትወዳለህን፡ ምንም እንኳ ሰው በየቀኑ... ክፉ ቢያደርስብህ ጭምር፡ እግዚአብሔርንስ ትወዳለህን? እንደ መጋዝ፡ "ህምምም!" እያልክ የምትጮኽ ከሆንክ፡ መንፈስ ቅዱስ ከነበረህ፡ ከአንተ መለየቱ ያሳያል፡

116 ተመልከቱ፡

> ... **ከሥራዋቿ ንስሐ** ባትገባ።
>
> **ልጆችዋንም በሞት እገድላቸዋለሁ፡...**

117 “ልጆቿንም፡” የኤልዛቤል ልጆች። ከዚያስ፡ ኤልዛቤል ምን አደረገች? ልጇን ወዲያ ማዶ፡ በይሁዳ ዘንድ ከሚገኘው (የይሁዳ) ባለስልጣን ዘንድ ዳረቻት። አሁን መንፈሳዊ ትግበራዉን በደንብ ተከታተሉ። ምናልባትም በስዕል ላስቀምጠው እችላለሁ። እዚህ ጋር፡ አሁን በደንብ ተከታተሉኝ፡

118 እነሆ ኤልዛቤል፡ እና እስራኤል **እዚህ ጋር** ናቸው። **እዚህ ጋር** ግን ይሁዳ አለ፡ እዚያ ማዶ፡ ከእነርሱ የተለየ ነገር ያለው ነው፡ ይህም **እዚህ ጋር** ኢዮሳፍጥ ይኖራል። በጣም ጥሩ። አሁን፡ **እዚህ ጋር** አክዓብ ነበረ፡ **እዚህ ጋር** ይኸው ኤልዛቤል ትኖራለች። ስለዚህ፡ **እዚህ ጋር** መጥታ እስራኤልን በሙሉ በጣዖት አምልኮ እንዲወድቁ አደረገቻቸው።

119 የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ያኔ በዘመኗ ያደረገችውም ቆስጠንጢኖስ ኒቆላውያንን (**እዚህ ጋር** ያሉቱ ቀዝቃዞች እና ተራዎች) ሁሉ አንድነት እንዲኖራቸው በማድረግ ከ—ከ—ቤተክርስቲያኒቱ ጋር እና ከአረማዊነት ጋር አንድ ባደረጋቸው ጊዜ፡ የአረማዊ መልክ የያዘ ክርስትና በስራ ጊዜ እንዲሁ ፈጸመች። የካቶሊክ ሰዎች ሆይ፡ ስሜታችሁን መጉዳት አልፈልግም፡ በእግዚአብሔር ፊት ግን ተጠያቂ ነኝ። የካቶሊክ ቤተክርስቲያን፡ አጉል እምነቶች፡ እና ጣዖታት፡ እና ሌሎች ነገሮች ሁሉ ያሉበት፡ አረማዊ የክርስትና አይነት ብቻ ነው። ይህ ትክክክል ነው፡ አረማዊ ቅርጽ ብቻ ነው። አሁን፡ ይህ እውነት ነው። በዚህች ደቂቃ ብሞት እንኳ፡ እውነቱ ይህ ነው። ፕሮቴስታንቶችም እንዲሁ በሌላ ምድብ ቢሆኑም፡ ያው ናቸው።

120 አሁን ኤልዛቤል ያደረገችውን ተመልከቱ። ደግሞ፡ ተመልከቷት፡ ለ—ለስይጣን... በጣም ስለተገዛች፡ ሴት ልጇቿን ወሰደች። **እዚህ ጋር** የተወለደች ሴት ልጅ ነበረቻት፡ ይህችኛዋ ሴት ልጇም **እዚህ ጋር** ለሚኖረው ቅዱስ እና ታላቅ ሰው ለልጁ ተዳረች፡ እና ከኢዮሳፍጥ ወዲያ ማዶ፡ **እዚህ ጋር** የነበረው ተመሳሳይ ነገር ወደዚህ ጎትተው አመጡ።

121 ማለት፡ ትክከለኞቹ ኒቆላውያን፡ ኒቆላውያኖቹ፡ ድርጅቱን የሚወዱ ተራ እና ቀዝቃዞቹ፡ **እዚህ ጋር** ካለው ነገር ጋር ተጋቡ። አሁንም አስተውሉ ተመሳሳይ ነገር። **እዚህ ጋር** ኤልዛቤልን ተቀበሉ ማለት (የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያንን)፡ ደግሞ **እዚህ ጋር** ልጇን ይዛ ማለት (ድርጅቶች) ከእነርሱ ጋር እንዲጋቡ አደረገቻቸው፡ እነርሱ ጋርም ተመሳሳይ ነገር ፈጸመችባቸው። “ልጆቿን በሞት እገድላለሁ፡” በመንፈሳዊ ሞት። እራሳቸውን ለሞት አደራጁ፡ መጀመሪያ የሆነባቸው ነገርም፡ መንፈሱ ትቷቸው ሄደ።

122 እስኪ ንገሩኝ። አንድ ነገር ልጠይቃችሁ፡ እዚህ ያላችሁ፡ እኔ የማውቃችሁ የተቀመጣችሁ አምስት ወይም ስድስት የታሪክ ምሁራን አላችሁ። መጥታችሁ አንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ወይም—ወይም አንድ የታሪክ—ጽሑፍ አሳዩኝ፡ ወድቀው ድርጅት ወደ መሆን የተመለሱ እንደገናም በሪቫይቫል የተነሱ አብያተ ክርስቲያናት ካሉ እንድታሳዩኝ እፈልጋለሁ። እስኪ ንገሩኝ። እራሳቸውን ባደራጁ ጊዜ፡ ከተደራጁ በኋላ ሪቫይቫል ኖሯቸው ያውቃልን? በጭራሽ፡ አያውቅም! መንፈሱ ትቷቸዋልና። ጴንጤዎቹንም ጨምሮ።

123 የጴንጤቆስጤ ቀን በረከት በወረደ ጊዜ፡ ሁላችሁም በልሳኖች ተናግራችሁ ነበር፡ እናንተም አናጋፋዎች-ላይ፡ የጴንጤቆስጤ በረከቶች እና ሌሎች ነገሮች፡ ወርዶባችሁ ነበር። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ግን ጠቅላይ ሞክር ቤት አቋቋማችሁ።

ሕብረት ማድረግ መልካም ቢሆንም፡ ድርጅት ግን አይገባም። አንድ ነገር ግን እወቁ፡ ይህን ልትቋቋሙ አይቻላችሁም፡ ወደ ኋላ ተመልሳችሁ እራሳችሁን በማደራጀት "የሰይጣን... ልጆች፡" መሆናችሁ አይቀርምና።

124 ከዚያ በኋላም የኢየሱስ ክርስቶስ ስም በተመለከተ፡ ሌላ ብርሃን መጣ። እነርሱም ደግሞ በሙሉ-ተጠምደው፡ እንዲህ ማለት ጀመሩ፡ "እግዚአብሔር ይመስገን፡ የኢየሱስ ስም ካልተቀበላችሁ፡ ገሃነም ትገባላችሁ። እኛ ተቀብለነዋል፡ እናንተ ግን አልተቀበላችሁትም።" እነርሱስ ምን ሆኑ? እዚያው ሜዳቸው ላይ ሞቱ፡ በነበራቸው ነገር ድርጅትን አቋቁመዋልና። አያችሁ? ብርሃኑ በቤተ ክርስቲያኒቱ እንዲመላለስ መፍቀድ ሰትችሉ፡ ድርጅታዊነት ወድያውኑ ሰፍራውን ተክቷል። እናንተ ግን እራሳችሁን አደራጃችሁ። ይህስ ምንድነው? የኤልዛቤል ልጅነት። ሁሉም በአንድነት፡ ሞተዋል።

125 አሁን አንድ ነገር ልጠይቃችሁ። አሴምብሊስ ኦፍ ጋድ፡ ወይም ዋንነሶች፡ ወይም—ወይም ሌሎች ማናቸውም በታላቅ የሕብረት ሪቫይቫል ትንሳኤ ኖሯቸው ያውቃልን? በጭራሽ አያውቅም! ይህ በቅርብ ጊዜ ያለፈ ሪቫይቫል፡ በወንዙ ዳር ላይ መንፈስ ቅዱስን የወረደበት የ1933፡ መነቃቃት (ዛሬም ብዙዎቻችሁ ጉባኤው ውስጥ ተቀምጣችኋል)፡ ያኔ የመጣው ታላቅ የፈውስ ጉባኤ፡ "ዓለምን ሁሉ ያጥለቀልቃል፡" የተባለለት ሲሆን፡ ከየትኛቹም ልዩ ልዩ የድርጅት ዓይነቶች የተነሣ አይደለም። እግዚአብሔር ከጽንፈ ዓለም ወጥቶ፡ ይህን ሪቫይቫል ለማስጀመር፡ ከሞላ ጎደል አረማዊ የሆነ ሰው አስነሳ። አሁንም ውጤቱን ተመልከቱት! አያችሁ?

126 ድርጅቶች ሁሉ፡ የተደራጁ ለታ፡ ይሞታሉ። "ልጆቿን በሞት እገድላቸዋለሁ፡" አለ። ኦህ፡ ማይ! አውቃችኋለሁ... እባካችሁ አትሰናከሉብኝ፡ እነሆ እኔ... ይህን እያወቅኩ ባልነግራችሁ፡ እጅግ-ወራዳ ግብዝ ሰው እሆናለሁ፡ እግዚአብሔርም ይጠይቀኛል። እንደ ጳውሎስ "የእግዚአብሔርን ምክር ሁሉ የማያስቀርባችሁ፡" አሆን እፈልጋለሁ። በትክክል። እሺ ይሁን። እሺ ይሁን።

127 ከዚያ በኋላ፡ በኢየሩሳሌም ዘንድ መሰውያዎችን አቆሙ። አሁን ማየት የምፈልገው... ኤልዛቤል ከአክዓብ ጋር በተጋባች ጊዜም፡ ይሰግዱላቸው ዘንድ ወደ እስራኤል ምስሎችን አመጣችላቸው። የኒቆላውያን አስተምህሮም እንዲሁ አደረገ፡ ከአረማዊነት ጋር በተጋባ ጊዜ፡ ጁፒተርን ወሰዶ፡ በጴጥሮስ፡ እና በቬኑስ፡ በማርያም ለወጡ፡ መጽሐፍ ቅዱስ እንዳለም፦ "እስራኤልን ሁሉ እንዲስቱ አደረገች።"

128 የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያንም ኤልዛቤል በልጇ ላይ እንዳደረገችው ሴቶች ልጆች ሁሉ፡ ከድርጅት ጋር እንዲጋቡ አድርጋቸዋለች፡ ነገሩ ሁሉ ኃጢአት ነው። እሺ እንግዲህ። ይሁን ሁሉ ተደርጎ የሰልጣን ተዋረድ በተዘረጋ ጊዜና፡ ፖፕ ቦኒፌስ—ፖፕ ቦኒፈስ ሳልሳዊ ዙፋን ላይ በተቀመጠ ጊዜ፡ ዙ—ዙፋን ላይ የተቀመጠ አምላክ ሆነ፡ ከዚያ በኋላ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ቦታ አልነበራቸውም። እውነት ነው። የእምነት መግለጫዎቻቸውን እና ፎርማሎቻቸውን፡ ይዘው ቀጠሉ።

129 ድርጅቱም ያንኑ ዶግማ ሲቀበል፡ የመንፈስ ቅዱስን ነፃነት ከቤተ ክርስቲያን ረግጠው አወጡት፡ ባፕቲስት፡ ፕሪስባይቴሪያን፡ ሜቶዲስት፡ ወዘተ። በእርግጥ ይህን አደረጉ! ኢየሱስ ስለ ወይን ግንድ እንደተናገረው ቀስ በቀስ ሲጠወልጉና

ሲሞቱ እናያቸዋለን። ስለዚህ፡ የመንፈስ ቅዱስ ድንቆች እና ምልክቶች በሙሉ ጊዜ ያለፈባቸው ናቸው ተባለ። እንደ እሷም፡ ሀብታም ሆነዋል። እርሷ እና ልጆቿም፡ ወደ ምድር ሁሉ ደርሳለችና፡ ዓለምን ሁሉ እንዲሰት አድርጋለች። እውነት ነው።

130 አሁንም በሌላኛው የቤተክርስቲያን ዘመን ሲጠራት ተመልከቱት። ሲጠራት ተመልከቱት። እዚህ መጨረሻ ላይ ሲማፀን፡ እና ቅሪቶችን ሲያወጣ ተመልከቱት፡ ስለ ጥቂቶቹ፡ "ስለ ምርጦቹ፡" እንዲህ ባይሆን... ስጋ ለባሽ ሁሉ ባልዳነም ነበርና።

131 በራዕይ 13፡6 እንደ ተጻፈ። ይህ ሁሉ በአንድ ደቂቃ ለማየት ጓጓችሁ አይደል? እንዲህ ብሏል... ማለት "ሴቲቱ (አውሬው) ሰዎች ሁሉ ምልክቱን እንዲቀበሉ አሰደርጎአቸዋል፡ (ድሆች እና ታላላቆች፡ ሁሉም ወገኖች)፡ ምልክቱን ማለት፡ የአውሬውን ምልክት እንዲቀበሉ አድርጓቸዋ፡" ይህም የሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ነው።

132 ያም ወይም ደግሞ የሰሩት ምስል... ራእይ 13:14፡ ለአውሬው ምስል ሠሩ። እ—እናንተም... ሁላችሁ ያንን እንዳነበባችሁት እገምታለሁ። ካላነበባችሁት ግን፡ በቀጥታ፡ ሄደን እናነባለን። የዮሐንስ ራእይ 13:14፡

> **በእነዚያም ተአምራት** በ**ምድር የሚኖሩትን ሁሉ** አሳታቸው **በአውሬው ፊት ይህን ሊያደርግ ሥልጣን አለውና፡** (ይህም የቤተክርስቲያን ኮንፌዴሬሽን ነው።)... እና **በአውሬው ፊት ማድረግ፡** በ**ምድር ላይ** በ**ሚኖሩ ወገኖች ሁሉ፡** ለ**አውሬው ምስል እንዲሠሩ ይናገራቸዋል፡** ለሞት **የሚያደርስ ቁስል** ነበረው (አረማዊነት)... ያም **በሰይፉ** ነው፡ እና (በጵጵሰና፡ በአረማዊት ሮም በጳጳሳዊት ሮም። አያችሁ? ) **በህይወት ኖረ**...

133 "ለእሷ የሚሆን ምስል ቢሰሩ።" ምን አይነት ይሆናል? ልክ አሁን እያደረጉ ያሉት፡ ቁርጥ አንድ ነው፡ የአብያተ ክርስቲያናት ህብረት ውስጥ ይንቀሳቀሳል፡ "አብያተ ክርስቲያናት በሙሉ የዚህ ድርጅት አባል ናቸው፡ ሁሉም ወደ አንድ ቡድን ውስጥ ይገባሉ።" አሁን መጽሐፍ ቅዱስ በመስራት ላይ ናቸው። ፖፕ ጆን ሁሉም ወደ አንድነት እንዲመጡ ግብዣ አቅርበውላቸዋል። የካንተርቤሪ ሰበካ፡ ሁሉም ተቀላቅለውበታል። እንደሚታወቀው፡ ከሁሉ አስቀድመው ወደ **ማሚ** ይመጣሉ፡ ምክንያቱ ክጅምሩ ጀምረው አመንዝሮች ናቸውና። አያችሁ? "ሁላችንም ኮሙኒዝምን ለመዋጋት በአንዲት ትልቅ አካል ጥላ ስር እንሆናለን፡" ይላሉ። ኮሚኒዝምን ያስነሳው ራሱ እግዚአብሔር መሆኑን አያውቁም (በዚህ መጽሐፍ ቅዱስ ላረጋግጥላችሁ እችላለሁ።) በምድርም ላይ ያፈሰሱትን የቅዱሳንን ደም ይበቀሉ ዘንድ፡ በልባቸው ውስጥ ይህን አኖረ። እስራኤልን ለመቀጣት እግዚአብሔር ንጉሥ ናቡከደነፆርን እንዳደራጀ ሁሉ— አሁንም ኮሚኒዝምን አደራጅቷል። ኮሙኒዝምን አደራጅቷል፡ እነሆም አንድ ቀን ሮምን ከካርታው ላይ በሞት ትጠራርጋታለች። [በቴፕ ላይ ባዶ ቦታ—እርታዒ።] በትክክል እውነት ነው። እግዚአብሔርም ተናግሯልና። ትክክል ነው።

እኔም ኮሚኒዝምን እቃወማለሁ፡ ፀረ-እግዚአብሔር ነውና። በትክክል። ነገር ግን ለዚያ ለባለ ብረት መጋረጃ ያን ያህል ትኩረት አትስጡ፡ ነገር ግን

ለባለ ሐምራዊ መጋረጃ ትኩረት ሰጡበት። **ፎክስስ ቡክ ኦፍ ማርቲይርስ** መጽሐፍ አንቡቡት እና ማየት ትጀምራላችሁ፡ በትክክል።

134 አሁን የት እንዳለን እንይ... እና ከዚያ በኋላ እዚህ እንደምታዩት (ባለጸጎች፡ ድሆች) ሁሉ ምልክት እንዲቀበሉ እንዳደረገች ታያላችሁ፡; እሷ ልትነካው የማትችለው አንድ መንጋ ግን አለ። ታውቁታላችሁን? ራእይ 13፡... 8።

135 ይሄን ስሙት። ላንበው፡

**እነሆም በባሕር** አሸዋ **ላይ ቆምኩ፡ አንድም አውሬ ከባሕር ሲወጣ አየሁ፡ አሥር ቀንዶችና ሰባት ራሶች ነበሩት፡... በቀንዶቹም** ላይ፡ **አሥር ዘውዶች... በራሶቹም** ላይ **የስድብ ስም ነበረ።** (ይህ ሰባቱ ተራራዎች ናቸው፡ ትናንት ማታ ሁሉንም ተምረናቸዋል፡ እና።)

ያየኹውም **አውሬ ነብር ይመስል ነበር፡ ... እግሮቹም** እንደ—ድብ **እግሮች፡ አፉም... እንደ አንበሳ አፍ ነበሩ፡ ዘንዶውም** (ይህም በሴቲቱ ፊት ልጇን ሊበላ በሴቲቱ ፊት ቆሞ የነበረው ቀይ ዲያብሎስ ነው፡ እርሱም ሮም፡ ነበረ ሁላችንም እናውቃለን።) ... **ኃይሉንና፡ ዙፋኑን፡ ትልቅም ሥልጣን... ሰጠው።**

**ከራሶቹም ለሞት እንደ ታረደ** ሆኖ **አንዱን አየሁ፡** (አረማዊነት፡ አያችሁ) **ለሞቱ የሆነውም ቍስል ተፈወሰ፡** (ጳጳሱ ቦታውን ያዘ፡ ከኒቆላውያን ጋር ከክርስትና፡ ጋር አንድ ሆነ) **ምድርም ሁሉ አውሬውን እየተከተለ ተደነቀ።**

136 ካቶሊካዊነት ከሰማይ በታች ባሉ ህዝቦች ሁሉ ውስጥ ተጥለቅልቀዋል። ትክክል ነው። ዳንኤልም ከብረት ጋር ስለሚቀላቀለው ሸክላ፡ እና የመሳሰሉትን ተናግሯል።

137 እኔም በዛ ላይ፡ በ "ብረት እና ሸክላ" ላይ ትንሽ ነገር ልበላችሁ። አስተውላችኋል፡ ወይስ ነግሬአችሁ እንደሆነ አላውቅም፡ በባለፈው እዚህ በተካሄደው ታላቁ ስብሰባ ላይ ክሩሼቭ ጫማውን አውልቆ ጠረጴዛውን በጫማ ሲደበድብ ትዝ ይላችኋል? አምስት የምስራቃዊ አገሮች፡ እና አምስት የምዕራባውያን አገሮች በዚያ ላይ ተሰብስበው ነበር፡ ክሩሼቭ የምስራቃውያን አገሮችን መሪ ሲሆን፡ አይዘንሃወር የምዕራባውያን አገሮች መሪ ነበር፡ ሁለቱ ዋና መሪዎች፡ ሁለቱ አውራ ጣቶች እነዚህ ነበሩ። በሩስያኛ፡ **ክሩሼቭ** ማለት፡ "ሸክላ" ማለት ነው። **አይዘንሃወር**፡ ማለት በአሜሪ-... በእንግሊዘኛ፡ "ብረት" ማለት ነው። ፍጻሜው ላይ ደርሰናል።

**ለዘንዶውም ስገዱለት ለአውሬው ሥልጣንን ሰጥቶታልና፡ እና**... (ይህ በተበርናክሉ ቀጣይ መልእክታችን ነው፡ ገባችሁ።)... **እንዲህ እያሉ፡ ስገዱለት፡ አውሬውን ማን** ይመስለዋል? **እርሱን**ስ **ሊዋጋ ማን ይችላል**?

138 በሌላ አነጋገር፡ ወደዚህ ተመልከቱ። አይዘንሃወር—እዚህ ዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ ትልቅ ስም ነበረው፡ በሮም ውስጥ ግን ተራ ነው፡ በሩሲያ ውስጥ፡ ተራ ነው። ክሩሼቭም በሩሲያ ውስጥ ታላቅ ሰው ነው፡ በዩናይትድ

ሰቴትስ ውስጥ ግን ተራ ነው። በሄደበት ታላቅ የሆነ ሌላ ሰው አለ፡ እሱም ጳጳሱ ነው (በትክክል።) “ራሳችንን በአንድነት አደራጅተን፡ እንሰባሰብ።”

**ታላቅንም ነገርና**... ስድብን የሚናገርበት **አፍ ተሰጠው**፡... **በአርባ ሁለት ወርም እንዲሠራ ሥልጣን ተሰጠው።**

**እግዚአብሔርንም** ለመሳደብ **አፉን ከፈተ**፡ (እና “የሰዎችን ስርዓት የሆነ ትምህርት ያስተምራሉ፡ ከዳተኞች፡ ችኩሎች፡ በትዕቢት የተነፉ፡ ተድላን የሚወዱ ይሆናሉ፡ የአምልኮት መልክ አላቸው ኃይሉን ግን ክደዋል”) ... **ስሙንም** ሰደበ፡ (ከ “ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ” ይልቅ “አብ፡ ወልድ፡ መንፈስ ቅዱስን” ወሰደ። አያችሁ? ) **ስሙንና ማደሪያውንም፡ በሰማይም**—የሚያድሩትን **ሊሳደብ... አፉን ከፈተ።**

**ቅዱሳንን**ም **ይዋጋ ዘንድ፡** (እነሆ ሰደት ይነሳልና) **ድልም ያደርጋቸው ዘንድ ተሰጠ**ው፡ በነገድና በወገንም በቋንቋም፡ በሕዝብም ሁሉ ላይ፡... ሥልጣን ተሰጠው።

**በምድር—በምድርም የሚኖሩ** ሁሉ **ይሰግዱለታል፡ ከዓለምም ፍጥረት ጀምሮ በታረደው በግ ሕይወት መጽሐፍ ስሞቻቸው** ያልተጻፉ **በምድር የሚኖሩ ሁሉ ይሰግዱለታል።** (ኦህ፡ ኦህ፡ ኦህ፡ ኦህ፡ ኦህ፡ ኦህ፡ ኦህ።)

139 “ከዓለምም ፍጥረት።” ስሞቻችን፡ በመጽሐፉ ውስጥ ከነበሩ፡ የተጻፉት ድሮ ናቸው። ኢየሱስም፡ “አባቴ አስቀድሞ ከሳበው በቀር ወደ እኔ ሊመጣ የሚችል የለም፡ አብም **የ**ሰጠኝ ሁሉ ወደ እኔ ይመጣል። በጎቼ ድምፄን ይሰማሉ ብሏል፡” (ምግቡ ይህ ነው፡ አያችሁ።) “የሌላው ግን... ”

140 ሌላው ግን እንዲህ ሊል ይችላል፡ “እኔም’ኮ፡ የቤተ ክርስቲያን አባል ነኝ፡ ልክ እንዳንተ ጥሩ ነኝ።” ይህ የበግ ምግብ አይደለም።

141 የበግ ምግብ **እነሆ**፡ “በክርስቶስ በሰማያዊ ሰፍራ አንድ ላይ መሰባሰብ ነው።” አቤት፡ እንዴት ድንቅ ነው! አይደለምን? በጣም ጥሩ።

142 አዎን፡ አሁን በፍጥነት እንጨርስ፡ ምክንያቱም ጊዜው እየመሸ ነውና። በጣም ጥሩ። “እኔ ግን እላለሁ።... ” አሁን እንየው፡ 23ኛው ቁጥር ደርሻለሁ

**ልጆችዋንም በሞት እገድላቸዋለሁ፡ አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ኩላሊትንና ልብን** የምመረምር **እኔ እንደ ሆንሁ ያውቃሉ፡ ለእያንዳንዳችሁም እንደ ሥራችሁ እሰጣችኋለሁ።**

**ዳሩ ግን ይህን ትምህርት** ለማትይዙ **ሁሉ፡ ለእናንተ፡ በትያጥሮን ለቀራችሁት እላለሁ፡...** (ምን ዓይነት ትምህርት ነበር? ድርጅት፡ ሊቃውንት፡ ሊቃነ ሊቃውንት፡ እና ጳጳሳት፡ ተመልከቱ።)

143 “ይህ ትምህርት ለሌላቸው።” አሁን፡ ከመጽሐፍ ቅዱስ፡ ትናንት ማታ እንዳየነው፡ እስራኤላውያን በሞዓብ በኩል ሲመጡ፡ አገር እንዳልነበሩ አይተናቸዋል። በምድር ፊት ላይ የሰፈረ፡ ነጻ ህዝብ፡ እንደነበረ አይተናል። ልክ ነው? በድንኳኖች እና በሌላ ነገሮች፡ የሚንከራተቱ ነበሩ፡ ጥላ ነው።

የጴንጤቆስጤ ወገኖችም በተመሳሳይ መንገድ እንዲህ ናቸው፡ እውነተኛው ጴንጤቆስጤ፡ ከቦታ ቦታ እየተንከራተተ ነው። አያችሁ? እሺ።

> ... እና ይህ **አስተምህሮ የላቸውም** (ግን እራሳቸውን አደራጅተው፡ ትልቅ ድርጅት በመፍጠር ላይ ናቸው) ... ይህ **ለሌላችሁ**... **የሰይጣንንም ጥልቅ ነገር እነርሱ እንደሚሉት ለማታውቁ ለእናንተ፡**...

144 የሰይጣን ዙፋን የት እንዳለ ማወቃችን አስታውሱ። ትናንት ማታ ወደ መጀመሪያው መልሰነው ነበር። የመጀመሪያው ዙፋኑ የት ነበር? ባቢሎን። ባቢሎንም... የባቢሎን ንጉሰና-ካህን፡ የነበረ—ባለ ስልጣን፡ ድል እያደረጉ የመጡ ከለዳውያን ባሳደዱት ጊዜ፡ ወደ ጴርጋሞን መጥቶ ዙፋኑ በዚያ አደረገ። እነሆ፡ ዙፋኑን ከሰናዖር ምድር ወደ ጴርጋሞን አዞረ። ትናንት ማታ በታሪክ ውስጥ በትክክል አንብበናል። በዚያም ሆኖ እነሆ፡ አሁንም የባቢሎን እናት የሆነች፡ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያንን መመሰረት ጀመረ። በጣም ጥሩ፡ “የሰይጣን ዙፋን።”

> ... ሲናገሩም **የሰይጣን** ዙፋን፡ **እንደሚሉት፡** ሌላ ሸክም **አልጭንባችሁም**።

145 “ያላችሁን ብቻ ጠብቁ እንጂ፡ ሌላ ሸክም አይኖርም።” ይህች በጨለማው ዘመን በጽኑ መከራ የነበረች፡ አያችሁ፡ ታናሺቱ መንጋ ናት። አሁን በዚያ ያለፉት ወደ አንድ ሺ አምስት መቶ ዓመታት ገደማ ነው።

> **ነገር ግን እኔ እስክመጣ ድረስ** ያላችሁን **ጠብቁት።** (በሌላ አነጋገር፡ “የጴንጤቆስጤ በረከት አሁንም በልባችሁ ውስጥ ይኖራል ነው። እፎይታን ልሰጣችሁ እስክመጣ ድረስ አጥብቃችሁ ያዙ፡ ምክንያቱም ይህ የሚቀጥለው ዘመን በሚቀጥለው ጊዜ እየመጣ ነውና።”)

> ... **ድል ለነሣው፡** ቃሌንም **እስከ መጨረሻ የሚጠብቅ፡ እኔ በአሕዛብ ላይ ሥልጣንን እሰጠ**ዋለሁ፡

> **በብረትም በትር ይገዛቸዋል፡** እኔ **ደግሞ ከአባቴ እንደ ተቀበልሁ፡** እንደ **ሸክላ** ዕቃም **ይቀጠቀጣሉ።**

146 አያችሁ፡ ያቺ ቤተክርስቲያን፡ ያቺ የጨለማ ዘመን ቤተክርስቲያን በፍርድ ላይ አረማዊት በነበረች መንጋ ላይ በተነሳች ጊዜ... ምን ይውጣት ይሆን? በደንብ ይቀጠቀጣሉ! እላችኋለሁ፡ የነሐስ እግሮች ይረግጣቸዋል! “በመቀጥቀጥ ይሰባብራቸዋል፡” ይላል መጽሐፉ።

> **የንጋትንም ኮከብ እሰጠ**ዋለሁ**።** (ይህ ምን እንደሆነ ታውቃላችሁ፡ አይደል? “የንጋት ኮከብ” ክርስቶስ ነው። በጣም ጥሩ።)

> **መንፈስ ለአብያተ ክርስቲያናት የሚለውን፡ ጆሮ** ያለው **ይስማ።**

147 ኦህ፡ ማይ! ደስ አይላችሁምን? ትንሸ መሸቶብናል። ተጨማሪ ትንሸ ይቀረኛል፡ ስለ ሁለቱ ሺ ዓመታት በተመለከተ፡ ምናልባት ነገ ማታ እዳስሰዋለሁ።

እርሱ ግን የሸለቆው አበባ ነው፡ ብሩህ እና የንጋት ኮከብ፡
ከእእላፋት ይልቅ ለነፍሴ የሚሻላት።
የሸለቆው አበባ፡ በእርሱ ብቻ አያለሁ፡
የሚያስፈልገኝ በሙሉ... ሙሉ የሚያደርገኝ።
በኀዘን መጽናኛዬ፡ በችግር ጊዜ ማረፊያዬ ነው፡
የሚያስጨንቅህን በእኔ ላይ ጣለው ይለኛል።
ሃሌሉያ!
የሸለቆው አበባ፡ ብሩህ እና የንጋት ኮከብ፡
ከእእላፋት ይልቅ ለነፍሴ የሚሻላት።

148 ትወዱታላችሁ? ኦህ፡ እኔ'ማ፡

እወደዋለሁ፡ እ...

አሁን እናምልከው፡ የሚቆራርጡ ቃሎቹ እና መልዕክቶቹ ናቸው።

እርሱ ወዶኛልና
መዳኔንም በቀራንዮ
በዛፉ ላይ ገዝቶልኛልና።

149 አይደንቅም ወይ! እወደዋለሁ። እንግዲህ፡ ያልዳሰስኳቸው ነገሮች በሙሉ፡ መጽሐፉ ላይ ታገኙታላችሁ፡ በርግጥም፡ በአንድ ምሽት የቤተ ክርስቲያን ዘመን በሙሉ መዳሰስ አንችልም። በዚህ ምሽት ጉሮሮዬ ስለ ሻከረ፡ በሰሱም ቢሆን ዝቅ አድርጌዋለሁ። ይሁን እንጂ፡ አቤት፡ አይደንቅም ወይ! ኦህ! እህምም!

ሰዎች በሁሉም ሰፍራ፡
ልባቸው በእሳት እየተነካ
የበዓለ ሃምሳው ነበልባል በልባቸው፡
አጥቦ ቀድሶ ያነጻቸው፡
ኦህ፡ አሁን በልቤ ውስጥ ይነዳል፡
ኦህ፡ ክብር ለስሙ!
አንዱ በመሆኔ ደስተኛ ነኝ።

ኦህ፡ አንዱ ነኝ፡ እኔም አንዱ ነኝ፡
አንዱ በመሆኔ ደስተኛ ነኝ፡ (ሃሌሉያ!)
አንዱ ነኝ፡ አንዱ ነኝ፡
አንዱ በመሆኔ ደስተኛ ነን።

150 ደስተኛ ናችሁ? አንድ ቀን ማታ ትዝ ይለኛል ከቻታኑጋ ሰመለስ፡ አውሮፕላኑ በሜምፊስ ቴ—ቴ—ቴነሲ ላይ፡ አርፎ ነበር። በዚያም ትልቅና ጥሩ ሆቴል ውስጥ፡ ተይዞልኝ ነበር። ደውለውም፡ "አውሮፕላኑ በሚቀጥለው ቀን በ— በሰባት ሰዓት ላይ፡ ይበራል፡" ብለውኝ ነበር።

151 እና ወደ ቤት እየመጣሁ እንደሆነ፡ ለአንዳንድ ጓደኞቼ በመጻፍ፡ ደብዳቤውን በፖስታ ሳጥን ውስጥ ለማስቀመጥ ጥቂት ደብዳቤዎች አዘጋጅቼ ነበር። እና እየወረድኩ ሳለሁ፡ መንፈስ ቅዱስ፡ "ቀጥል ተራመድ" አለኝ። እኔም ቀጠልኩ፡ እና ጥቁር ማሕበረሰብ የሚኖሩበት ቀበሌ ውስጥ ገባሁ።

152 በዚያም ቆሜ፡ "ወይኔ! ኧረ፡ አውሮፕላኑ የሚበርበት ጊዜ ደርሷል፡" አሰብኩኝ።

153 መንፈስ ቅዱስ ግን ደጋግሞ፡ “ቀጥል ተራመድ” ይለኝ ነበር። ልክ ባለፈው ቀን በጫካ ውስጥ እንዳደረገው ዓይነት፡ ነገር ነው። “ቀጥል ተራመድ።” ይለኛል ስለዚህ መሄዴን ቀጠልኩ።

154 እንደ አጋጣሚ ማዶ ላይ አሻግሬ አየሁ፡ እና ጥቁር ማሕበረሰብ የሚኖርባቸው ማዶ ላይ፡ ከነበሩ ጎጆዎች መካከል፡ አንደኛውን ምስኪን ጎጆ ተመለከትኩ። እና አሮጊትዋ እማማ ጀሚማ፡ ጭንቅላትዋ ላይ፡ የወንድ ሸሚዝ የሚመስል ነገር አስራ፡ እንዲህ... ተደግፋ ነበር።

155 ወደሷ አቅጣጫ እየሄድኩ እንዲህ እየዘመርኩ ነበር፡

እኔም... አንዱ ነኝ፡ አንዱ ነኝ፡
አንዱ በመሆኔ ደስተኛ ነን፡ (ኦህ፡ ሃሌሉያ!)

“**ጌታ ሆይ፡ ምን ትፈልጋለህ?**”

አንዱ ነኝ፡ አንዱ ነኝ፡

በመንፈስ መመራት ታምናላችሁ? አዎን፡ በትክክል።

አንዱ በመሆኔ ደስተኛ ነን።

156 የዛሬ አስራ አራት አመት ገደማ ይሆናል። እሱማ አጥር አጥሩን ታይ ነበር። ኦህ፡ ከሷ የአንድ መንደር ግማሽ ብሎክ ያህል፡ ርቄ ነበር፡ እና የሚገርማችሁ፡ ይህች ምስኪን ጥቁር እመቤት፡ እኔን ከማዶ እያየችን እንደሆነ አየኋት። እና፡ መዘመሬን ተውኩና፡ ጉዞዬን ቀጠልኩ፡ መጓዝ ጀመርኩ። ወደሷ ተጠጋሁ፡ እንባዎቿ በወፍራም ጉንጮቿ ላይ እየተንደባለሉ ይወርዳሉ፡ አየችኝ፡ እና እንዲህ አለችኝ፡ “እንደምን አደርክ፡ ፓርሰን!”

157 ዞር ብዬ፡ እንዲህ አልኩ፡ “እንደምን አሉ፡ የኔ እናት? ” እሳቸውም ተናገሩኝ... ዘወርም ብዬ፡ ይስቃሉ፡ ፊታቸው ላይ ትልቅ ፈገግታ ነበረ። እኔም “ፓርሰን መሆኔን እንዴት አወቁ፡” ብዬ ጠየቅኳት? አያችሁ፡ ወደ ደቡብ አካባቢ፡ **ሰባኪ** የሆነ ሁሉ “ፓርሰን” ብለው ይጠሩታል። እኔም... እንዲህ አልኩ፡ “ፓርሰን መሆኔን እንዴት አወቁ? ”

እሷም፡ “እንደምትመጣ አውቄ ነበር!” አለችኝ፡

እኔም፡ “እንዴት ልታውቂ ቻልሽ? እኔን ታውቂኛለሽን? ”

እሷም፡ “አይደለም፡ ጌታዬ፡” አለች። እና “እንደምትመጣ አውቄ ነበር” አለችኝ። “ስለ ሱነማዊቷ ሴት የሚናገረውን ታሪክ ሰምተህ ታውቃለህ፡” አለችኝ?

“አዎን፡ እመቤት፡” አልኩ።

158 እና እንዲህ አለችኝ፡ “እንግዲህ፡” “እኔም ያቺ ሴት እሷ ነኝ፡” አለችኝ። “ጌታ ህጻን ልጅ ሰጠኝ፡ እኔም... አሳድገዋለሁ ብዬ ቃል ገባሁ፡” አለችኝ። “ድሃ ሴት ነኝ። ኑሮን ለማሸነፍ የነጮች ቤት ውስጥ እያጠብኩ እተዳደራለሁ፡” አለችኝ። እንዲህ አለችኝ፡ “እርሱም እንደነገረኝ—ልጅ ሰጠኝ፡ እኔም አሳድገዋለሁ ብዬ ቃል ገባሁለት።” አለችም፡ “የቻልኩትን ያህል ምርጥ አድርጌ አሳደግኩት፡ ግን” አለች፡ “ፓርሰን ሆይ፡ የማይረቡ ወዳጆች ጋር መዋል ጀመረ። ህመም ይዞ መጣ፡ እኛም ስለ በሽታው የምናውቀው ነገር የለም።” “በሽታው የመጨረሻ ደረጃ ላይ ደርሷል። እነሆ አልጋ ላይ ነው፡ ለሞት ጣር ላይ ነው፡” አለችኝ።

“አሁን ራሱን ከሳተ፡ ሁለት ቀን ሆኖታል፡” አለችኝ። እንዲህ አለች፡ “የሕክምና-ባለሞያ ዶክተር መጥቶ፡ ‘ልቡን እና ሌላ አካሉ በልቶታል፡ ወደ ደም ስሩ ዘልቆ ገብቷል፡ አሁንም እጅግ ስለጎዳው፡ እኛ የምናደርግለት እርዳታ ምንም አይጠቅመውም ብሎኛል።’” “እየሞተ ነው፡” አለችኝ። አክላም “ኃጢያተኛ ሆኖ ሲሞት ማየት፡ እኔ አልችልም፡” አለችኝ። እና፡ “ጸለይኩ ጸለይኩ፡” “ሌሊቱን በሙሉ ስጸልይ አደርኩ፡” አለችኝ። “እራሱን ሰቷል፡ አሁን ምንም አያውቅም፡” አለች። “ለሁለት ቀናት ምላሽ የለውም፡” አለችኝ።

159 አለችም፡ “ጸለይኩ፡ እንዲህ ብዬ፡ ‘ጌታ ሆይ፡ ልክ እንደሱነማይቷ ሴት፡’ ‘ልጁን የሰጠኸኝ አንተው ነህ።’ አሁንስ፡ ‘ኤልያስህ ወዴት አለ? ወዴት ነው... ? ’ አልኩት፡ ‘እሺ፡ የት—የት እኔን የሚረዳኝ ወዴት አለ? ’”

160 እንዲህም አለች፡ “እንደተንበረከኩ የተኛሁ መሰለኝ።” እርሰዋም አለች፡ “ጌታ በሕልሜ፡ ተናገረኝ፡” እንዲህም አለኝ፡ “‘ወጥተሽ በሩ ላይ ቁሚ። እነሆም ጠቆር ያለ ሱፍ ለብሶ፡ ባለ ቆዳ ኮፊያ ሰው፡ በጎዳናው ወደ ታች እየወረደ ይመጣል።’ እነሆም እርሱ፡ ‘ከአንቺ ጋር ይነጋገራል’’’ አለኝ።

161 እኔም እነሆኝ፡ “ገና ጎህ ሳይቀድ እዚህ ቆሜአለሁ” አለችኝ። ጀርባዋ በጤዛ ረጥቦ ነበረ። እሷም “እነሆ የቆዳ ኮፍያ አጥልቀህ ስትመጣ አየሁህ፡” አለችኝ፡ “ነገር ግን ከዚህ ጋር ደግሞ አነስ ያለች ተንጠልጣይ ሻንጣ መያዝም ይጠበቅብህ ነበር፡” አለችኝ።

162 እኔም “ሆቴል ውስጥ ተውኩት፡” አልኳት። አያችሁ? እና እንዲህ አልኳት፡ “ልጅሽ አሞታል? ”

“እየሞተ ነው፡” አለችኝ።

እኔም እንዲህ አልኳት፡ “ስሜ ብራንሃም ነው፡” “እኔን ታውቂኛለሽን፡” አልኳት?

እሷም “አላውቅህም፡ ጌታዬ፡ ፓርሰን ብራንሃም፡ ስለ አንተ ሰ—ሰምቼ አላውቅም፡” አለችኝ።

“ለበሽተኞች እጸልያለሁ፡” አልኳት። ያ ግን ትዝ አላላትም። ልጇ እስከነ ኃጥያቱ እንዲሞት፡ አልፈለገችምና።

163 ወደ ውስጥ ዘለቅኩ፡ በዚያም በሩን እንዲመልስ የሆነ ነገር የተደገፈበት አሮጌ በር ነበራቸው (ምናልባት ብዙዎቻችሁ ስሜናውያን ምን እንደሆነ አታውቁትም)፡ ግን፡ በሩ እንዲዘጋ የሚያደርግ ነገር ነው። እና ወደ ቤት ዘልቄ ገባሁ፡ እነሆም ቤቷ፡ ባለ-ሁለት ክፍል፡ አነስ ያለች፡ ትንሽ ቤት ናት (በምስሉም ትንሽ... “ሾጣጣ” ብለን የምንጠራው አይነት ቤት ይመስላል) ቁጭ ያለ ነገር፡ ነው፡ **በዚህ** በኩል አንድ ክፍል አለ፡ ያ ደግሞ ሳሎን ነው፡ መኝታ ቤት፡ እና ሌላው ሁሉ በአንድነት፡ ኩሽናውም **በዚያ** ማዶ ላይ ይገኛል። ሰገባ... ትንሽ እና የታሸገች ነጭ ቤት፡ በጎን በኩል የተቦደሰች፡ በተጋደሙ ቦርዶች የተሰራች፡ ደስ የምትል ናት። እንግዲህ... ሌላም፡ ከጣሪያው አናት ላይ የሚጣበቅ ወረቀት እንደነበራት አምናለሁ፡ እንደ ጤዛ ያሉ ትልልቅ ጠብታዎች፡ በላዩ ላይ ተንጠልጥለው እንዳየኋቸው፡ አስታውሳለሁ።

164 ከዚያም ወደ ውስጥ ሰገባ፡ በሩ አጠገብ፡ “እግዚአብሔር ቤታችንን ይባርክ፡” የሚል የተንጠለጠለ ምልክት ነበረ። ጥግ ላይ አንድ አሮጌ አልጋ፡

አንዱ እዚህ እና እዚያ አለ። እነሆም ግዙፍ ሰው አልጋው ላይ ተጋድሞ ነበር (ወለሉ ላይ ምንጣፍ አልነበረም)፡ ልጁም ታላቅ እና ግሩም ነበር፡ ተለቅ ያለ ቆንጆ-ልጅ ተኝቷል። በእኔ ግምት... አንድ መቶ ሰባ ወይም ሰማንያ ፓውንድ ይመዝናል፡ ቁመቱም ስድስት ወደ ጫማ ይጠጋል። እና ብርድ ልብሱ እጁ ላይ ይዞ፡ "እህም። እህም፡" እያለ ያቃስታል።

165 እሷም "የእናቱ ልጅ፡" ብላ ጠራችው።

166 እኔም "'የእናቱ ልጅ፡'" ብዬ አሰብኩ። ቂጢኝ፡ የሚሉት ተላላፊ በሽታ—ነበረበት። እና ሞት አፋፍ—ላይ ደርሷል።

167 እሷም ግንባሩን ሳመችው እና፡ "የእናቱ ልጅ፡" እያለች፡ ዳበሰ ዳበሰ አደረገችው።

168 እንደው፡ ልቤ በኃይል አዘነ። እና አሰብኩት፡ "በርግጥ፡ ምንም ያህል በኃጢአት ብትሰጥምም፡ ልጇ ነህ።" "እያችሁ፡ ምንም ያህል መጥፎ ቢሆንም'ኳ፡ አሁንም፡ 'የእናቱ ልጅ' ነው፡" ብዬ አሰብኩ። ያን ጊዜ እንዲህ አሰብኩ፡ "እግዚአብሔር ሲናገር፡ 'እናት ያጠባችውን ልጇን ትረሳ ይሆናል፡ እኔ ግን ሰምህ በእጄ መዳፍ ቀርጬዋለሁና፡ መቼም ልረሳህ አልችልም።'" እያችሁ? ሊሆን አይችልም!

169 ምስኪኗ አሮጊት ወዲያ ወዲ ሰትንቆራጠጥ ተመለከትኳት። ወንድሜ ሆይ፡ ቤቷ ውስጥ ምንም እንዳልነበራት፡ ያስታውቃል፡ ነገር ግን በኢንዲያናም ይሁን በሌላ የሚገኙ ቤቶች ሁሉ ሊኖራቸው የሚገባ አንድ ነገር በቤቷ ውስጥ ነበራት፡ ያም እግዚአብሄር ነው። ቀጭ-ቋ የሚሉ ሴቶች፡ እና አሰቀያሚ የብልግና ነገሮች፡ የበዙበት ግዙፍ ቤት ከሚኖረኝ ያንን ቢኖረኝ እመርጣለሁ። ተከፍተው የነተቡ አሮጌ ገፆች ያሉት፡ ያረጀ መጽሐፍ ቅዱስ ያለበት ቤት።

170 አየኋት። እና "ማሪ፡ ሰባኪው ሊጸልይልህ መጥቷል፡" አለችው።

171 "እህህ። እህህ። ጨለማ። እህህ፡" አለ።

172 እኔም "ምን እያለ ነው፡" አልኳት?

"ምንም አያውቅም። ባለ-መድኃኒቱ ዶክተሩ እንዳለው፡ 'እራሱን ስቷል ብሎኛል፡'" አለችኝ። "በአንድ ሰፊ በሕር ላይ፡ ጀልባ እየቀዘፈ፡ በሆነ ሰፍራ እንደጠፋ አድርጎ ያሰባል፡" አለችኝ። እንዲህም አለች፡ "መቋቋም የማልችለው ነገር ይህ ነው፡ ፓርሰን፡ ልጄ እንዲህ ጠፍቶ፡ መሞቱን ማሰብ አልችልም።" "አንተ ልትረዳኝ እንደመጣህ አውቃለሁ፡ ምክንያቱም ጌታ ነገሩን ነግሮኛል፡" አለችኝ።

እኔም፡ "እሺ እጸልይለታለሁ፡" "ምናልባት ጌታ ይፈውሰው ይሆናል፡" አልኳት።

173 እሷ እርሱ ተነስቶ 'ድኛለሁ' ብሎ እንዲናገር ብቻ ትፈልግ ነበር እንጂ፡ በሌላ ነገር ላይ ፍላጎት አልነበራትም። ይዳንላት ብቻ እንጂ፡ ለሌላው ችግር የለባትም። ሰለዚህ፡ አንዳንዴ፡ እስከዳነ ድረስ፡ የትም ቢሄድ፡ ምንም ችግር የለውም! አቤት፡ እንዲህ አይነቱ አስተሳሰብ በኖረን! በዚያ በዘላለማዊው ቤት፡ አንድ ቀን ከእሱ ጋር አብራ እንደምትኖር አውቃለች።

"ብቻ 'ድኛለሁ' ብሎ ሲናገር ልሰማው፡" አለችኝ።

“እራሳችንን ዝቅ እናድርግ፡” አልኳት። ተንበረከከች። እና እግሩን ያዝኩት፡ እና እግሮቹ በጣም ቀዝቃዛ እና እርጥብ ነበሩ። እና የለበሰው ነገር በላዩ ላይ መሳብ አልቻልኩም፡ ትንሽ—ትንሽ ቀጭን ብርድ ልብስ በላዩ ላይ አልብሳው ነበረች፡ በዚያ ላይ፡ የለበሰው ቁምጣ ብቻ ነበር።

174 እና እሱ... በዚያ ውስጥ እንዳለ ስለሚያስብ፡ ያንን ወደ ኋላው ይጎትተው ነበር። ያንን ይዞ፡ መቅዘፊያን የሚጎትት ይመስለዋል፡ ደግጋሞ “እጅግ ጨለማ ነው። እህህ። እህህ። እጅግ ጨለማ ነው፡” ይል ነበር። ልታነጋግረው ሞከረች፡ እርሱ ግን እየጎተተ፡ “ጨለማ እና ብርድ ነው፡” ማለቱን ይቀጥል ነበር።

175 ከዚያም—ጥቂት ዝም ብዬ አየኋት፡ እና እዚያው እንደተንበረከከች፡ “እማማ፡ ጸሎቱን ትጀምሪልናለሽ ወይ፡” ብዬ ጠየቅኳት?

“እሺ፡ ጌታዬ፡” አለች።

176 በዚያች ክፍል ውስጥ የነበርነው፡ እኔ፡ እሷ፡ ልጁ እና፡ መንፈስ ቅዱስ ብቻ ነበርን። ያቺ ቅድስት ሴት ጸለየች። አቤት! እሱን ስታናግረው፡ ለብዙ ዘመን ከእርሱ ጋር ስታወራ እንደኖረች ይገባችኋል። አዎን፡ ጌታዬ! ከማን ጋር እንደምታወራ የምታውቅ ናት። “ጌታ ሆይ፡ አንተ ምን እንደምታደርግ እኔ አላውቅም፡” አለች፡ “አንተ ያልከው ሁሉ ግን እነሆ አሁንም ያው ነው፡” አለች።

177 ኦህ፡ ማይ! ኦህ! እነሆ ደስ ይለኛል፡ ያኔ ከቅዱሳን ጋር የነበረው ኢየሱስ አሁንም ያው ስለሆነ እደስታለሁ። ዛሬም ያው ኢየሱስ ነው።

178 ስለ ኃይማኖቷም፡ ባፕቲስት ትሁን፡ ጴንጤ ወይም ምንም ትሁን ምን፡ አልጠየኳትም። ያ የእኔ ጉዳይ አልነበረም። መንፈስ ቅዱስን ብቻ—እየተከተልኩ ነበር፡ እሷም እንዲሁ ታደርግ ነበር። ምን ሊሰራ እንደሆነ ለማየት ጉጉት አደረብን።

179 እና ተንበረከክን፡ እና መጸለይ ጀመረች። ጸሎቷን እንደጨረሰች፡ ተነስታ ጭንቅላቱን ሳመውና፡ “እግዚአብሔር፡ ልጄን ይባርክ፡” አለች።

180 ከዚያ በኋላ “ፓርሰን፡ አሁን አንተ ትጸልያለህን፡” አለችኝ?

181 እኔም “አዎን፡ እመቤት፡” አልኳት። ያን ጊዜ ስምንት ሰዓት ተኩል ሆኖ ነበር፡ ምናልባትም እሩብ ጉዳይ ለዘጠኝ፡ የነበርኩበት ርቀት—እስከ ቦታው ድረስ ሁለት ማይልስ ያህል ነበር፡ እና—እና የአውሮፕላኑ በረራ በሰባት ሰአት ነው፡ እኔም መቼ እንደምወጣ አላውቅም ነበር።

182 እጄን በእግሩ ላይ ጫንኩኝና፡ እንዲህ ጸለይኩ፡ “የሰማይ አባት ሆይ፡ ይህን አልገባኝም። እኔ—ቀደም ብዬ ወደ አውሮፕላን መሳፈር ይገባኝ ነበር፡ ምናልባትም ከአንድ ሰዓት ተኩል ቀደም ብዬ... አንተ ግን። ደጋግመህ ‘ቀጥል ተራመድ፡’ አልከኝ፡ እስከ አሁን የደረስኩበት ነገር ይህ ብቻ ነው። እሷ እንዳለችውም... ስመጣ እንዳየችኝ ተናግራለች። ጌታ ሆይ፡ ያ አንተ—አንተ ራስህ ከሆንክ፡ እጄን በዚህ ልጅ ላይ ከመጫን በቀር ምን ማለት እንደሚገባኝ አላውቅም።”

183 እንዲህ አለ፡ “ኦህ፡ እማዬ፡” “አሁን ብርሃን እየበራ ነው፡” ብሎ ተናገረ። ከዚያ ከአምስት ደቂቃ በኋላ፡ እናቱን በእጆቹ አቅፎ፡ አልጋው ጫፍ ላይ ቁጭ አለ።

184 ሾልኬ ወጣሁ፡ ሮጬ ታክሲ ያዝኩና፡ ሻንጣዬን ለመያዝ ወደ ሆቴሉ ቸኮልኩ። በእነዚያ ቀናት ምናልባት ሄጄ፡ አንድ ወይም ሁለት ቀን እጠብቅ ይሆናል እያልኩ አሰባለሁ። ያኔ ከጦርነቱ በኋላ አውሮፕላን ለማግኘት ምን ያህል ከባድ እንደነበረ ታስታውሳላችሁ፡ ስለዚህ “ሁለት ቀናት መጠበቅ አለብኝ፡” በማለት አሰብኩ።

185 እና ታክሲዬን ይዤ፡ ወደ ኤርፖርት በፍጥነት ወጣሁ። ልክ እንደደረስኩ፡ “የበረራ ቁጥር 196 ወደ ሉዊስቪል፡ ኬንታኪ፡ አሁን እየወጣ ነው፡” ይሉ ነበር። እግዚአብሔር ያንን አይሮፕላን፡ መሬት ላይ እንደዚያ ያዘልኝ። ኦህ፡ እንዲሁ እንደሆነ አምናለሁ!

186 ከዚያ ከሁለት ዓመት በኋላ ገደማ፡ በዚያ ዘንድ ጉባኤ ስለነበረ፡ ወደ አሪዞና፡ ወደ ወንድም ሻሪት ለመሄድ፡ በባቡር እየወረድኩ ነበር። እና ወንድም ሙርን እና ሌሎችን ጨምረን አብረውኝ መሄድ ነበረባቸው። ስለዚህ በዚያ በደረስኩ ጊዜ፡ ሜምፊስ ላይ ቆምኩ። ወደ ምዕራብ ሲሄድ እንዴት እንደሚቆም ሁላችሁ ታውቁት ይሆናል፡ እና ባቡሩ ይቆማል፡ ከዚያ በኋላ ሲወጣ ማዞሪያውን ይይዝና ያጠፋል።

187 እናም በባቡሩ ውስጥ የሚሸጡ ሳንድዊቾች፡ ለእያንዳንዳቸው ስድሳ ሳንቲም ይጠይቃሉ። እና ሌላ ቦታ በአስር፡ አስራ አምስት ሳንቲም፡ ልገዛቸው ልገዛቸው እንደምችል፡ ታውቃላችሁ። እና ጥቂት ሳንድዊቾች ለመግዛት፡ ባቡሩ እስኪቆም ድረስ ጠበቅኩት። አንድ ሳህን ሙሉ ሃ-... ሃምበርገር ለራሴ ገዝቼ፡ አመት በአል እያሰመሰልኩት ለመሄድ ጓግቼአለሁ። ዘልዬ ወጣሁና ሃምበርገር የሚሸጥበት ሱቅ ፍለጋ፡ በፍጥነት መሮጥ ጀመርኩ፡ ዙርያዬን ቃኘሁ፡ በዚያ የሚቆመው ለሰላሳ ደቂቃ ያህል ነው።

188 እና ለራሴ ሃምበርገሮችን መግዛት ጀ——ጀመርኩና፡ አንድ ሰው ሲጣራ ሰማሁ፡ “ሄሎ፡ እንዴት ነህ፡ ፓርሰን!” እና ዙሪያዬን ተመለከትኩ፡ ታውቃላችሁ፡ ትንሽ ቀይ ኮፍያ አርጎ፡ ቆሞ ዓይኖቹን እያርገበገበ፡ “አታውቀኝም፡ አይደል፡” አለኝ?

“የማውቅህ አይመስለኝም፡ ልጄ።”

ወደኔ ቀረበና፡ “በደንብ እየኝ!” አለኝ፡

እኔም አልኩት፡ “አቤት? ” እንዲህ አልኩት፡ “እኔ የማውቅህ አይመሰለኝም።”

እርሱም፡ “እኔ አውቅሃለሁ!” አለ፡ “አንተ ፓርሰን ብራንሃም ነህ!”

እኔም፡ “አዎን፡ ትክክል ነህ፡” አልኩት፡ “በሰብሰባዎቼ ውስጥ ተገኝተህ ታውቃለህ? ”

“አይደለም፡ ጌታዬ!” አለኝ፡ እንዲህም አለኝ፡ “ታስታውሳለህ የዛን ቀን ጠዋት ወደ ቤታችን የመጣህ ዕለት እናቴም ከ-... ? ”

“ኦህ!” “ብቻ አንተ እሱ ነኝ እንዳትለኝ!” አልኩት፡

እርሱም፡ “አዎን፡ እኔው ነኝ! አዎን፡ እኔው ነኝ!” አለኝ፡ “ፓርሰን፡” አለኝ፡ “አሁን ተፈውሻለሁ፡ ደስተኛ፡ እና ጤነኛ ሆኛለሁ። ይህ ብቻም አይደለም፡ አሁን ክርስትያን ሆኛለሁ!”

189 ጌታ ይመስገን! ኦህ!

ሰገነት ላይ በአንድነት ነበሩ፡
ሁሉም በሰሙ ሲጸልዩ፡
በመንፈስ ቅዱስ ተጠመቁ፡
ስለ ስራው ኃይል ተሞልተው፡
ያን ቀን ለእነርሱ ያደረገው
ለአንተም ያደርጋልሃል፡ (ደስ አይልህምን? )
አንዱ በመሆኔ ደስተና ነኝ።

አንዱ ነኝ፡ አንዱ ነኝ፡
አንዱ በመሆኔ ደስተና ነኝ፡ ሃሌሉያ!
አንዱ ነኝ፡ አንዱ ነኝ፡
አንዱ በመሆኔ ደስተና ነኝ።

ትልቅ ትምህርት እና ሌላ ነገሮች አልነበራቸውም፡

ምናልባት ያልተማሩ ቢሆኑ፡
በዓለም ትምክህት ባይኖራቸውም፡
ሁሉም በዓለ ሃምሳን ተቀብለዋል፡
በኢየሱስ ስምም ተጠምቀዋል፡
አሁን ሩቅም፡ ቅርብ ላሉ ሁሉ፡
ኃይሉ አሁንም አንድ ነው ይላሉ፡
አንዱ በመሆኔ ደስተና ነኝ።

አንዱ ነኝ፡ አንዱ ነኝ፡
አንዱ በመሆኔ ደስተና ነኝ፡ ሃሌሉያ!
አንዱ ነኝ፡ አንዱ ነኝ፡
አንዱ በመሆኔ ደስተና ነኝ።

ና፡ ወንድሜ፡ ይህን በረከት ተቀበል
ልብህን ከኃጢአት የሚያነጻ፡
የደስታ-ቃጭሎች ማስዘመር ይጀምራል
ነፍስህን ያነቃቃል፡
ኦህ፡ በልቤ ውስጥ እየነደደ ነው፡
ኦህ፡ ይሁን ክብር ለሰሙ፡
አንዱ በመሆኔ...

አሁን ከአንድ ሰው ጋር በፊት፡ ከኋላችሁ፡ እና በዙሪያችሁ ካሉ ሰዎች እጃችሁን ተጨባበጡ፡

ኦህ፡ አንዱ ነኝ፡ አንዱ ነኝ፡
አንዱ በመሆኔ ደስተና ነኝ፡ ሃሌሉያ!
አንዱ ነኝ፡ አንዱ ነኝ፡
አንዱ በመሆኔ ደስተና ነኝ።

አንዱ ነኝ፡ አንዱ ነኝ፡
አንዱ ነኝ በመሆኔ... ? ...
... ደስተኛ ነኝ፡
አንዱ በመሆኔ ደስተና ነኝ።

አንዱ ነኝ፡ አንዱ ነኝ፡
አንዱ በመሆኔ ደስተና ነኝ፡ ሃሌሉያ!
አንዱ ነኝ፡ አንዱ ነኝ፡
አንዱ በመሆኔ ደስተና ነኝ።

190 ይህ የጥንት-እምነት ምንድን ነው? ያኔ **እዚህ** የተጀመረ ነበረ፡ ከጫፍ እስከ ጫፍ ድረስ በኢየሱስ ደም ነጠብጣብ የተሞላች ናት። ኦህ፡ ማይ! ኦህ፡ ስለ ወንጌል እጅግ ደስ ይለኛል! ኦህ! ኦህ፡ አዎን፡ ወዳጄ!

ደሙ ያንጠባጥባል፡ አዎን፡ ደሙ ያንጠባጥባል፡
የመንፈስ ቅዱስ ወንጌል ደም ይንጠባጠባል፡
ለእውነት የሞቱ የደቀ መዛሙርት ደም፡ (የሰማዕት፡ እና የሁሉም)፡
የመንፈስ ቅዱስ ወንጌል ደም ይንጠባጠባል፡

አሁን፡ ይህ ወንጌል ምን አይነት ነው? በጴንጤቆስጤ የተጀመረው አይነት ነው፡ አያችሁ።

ለዚህ የመንፈስ ቅዱስ እቅድ መጀመሪያ የሞተው፡
መጥምቁ ዮሐንስ ነበር (እነሆ፡ በእናቱ ማኅፀን ውስጥ ሆኖ፡ የተቀበለው ነው፡ ታውቃላችሁ።)... እንደ ሰው ሞተ፡
በዚያን ጊዜ ጌታ ኢየሱስ መጣ፡ ሰቀሉት፡
መንፈስ ሰዎችን ከኃጢአት እንደሚያድናቸው ሰበከ።

ደሙን ያንጠባጥባል፡ አዎን፡ ደሙን ያንጠባጥባል፡
የመንፈስ ቅዱስ ወንጌል ደም ይንጠባጠባል፡
ለእውነት የሞቱ የደቀ መዛሙርት ደም፡
የመንፈስ ቅዱስ ወንጌል ደም ይንጠባጠባል።

ድርጅት ልትመሰሩትበት አትችሉም! ኧህ-ሃህ!

ጴጥሮስና ጳውሎስ፡ እና ዮሐንስ ዘመለኮት፡
ይህ ወንጌል እንዲያበራ ሕይወታቸውን ሰጡ፡
ከጥንት ነቢያት ጋር፡ ደማቸውን ቀላቀሉ፡
እውነተኛው የእግዚአብሔር ቃል በእውነት ይነገር ዘንድ።

ደሙ ያንጠባጥባል፡ አዎን፡ ደሙ ያንጠባጥባል፡
የመንፈስ ቅዱስ ወንጌል ደም ይንጠባጠባል፡
ለእውነት የሞቱ የደቀ መዛሙርት ደም፡
የመንፈስ ቅዱስ ወንጌል ደም ይንጠባጠባል።

ከመሠዊያው በታች፡ ነፍሳት ያለቅሳሉ “እስከመቼ፡”
እያሉ?
ጌታ በደለኞችን የሚበቀልበት፡
ነገር ግን የሕይወታቸውን ደም የሚሰጡ ብዙዎች ገና አሉ
ለመንፈስ ቅዱስ ወንጌል እና ለአለላው ጎርፍ።

ደሙ ያንጠባጥባል፡ አዎን፡ ደሙ ያንጠባጥባል፡
የመንፈስ ቅዱስ ወንጌል ደም ይንጠባጠባል፡
ለእውነት የሞቱ የደቀ መዛሙርት ደም፡
የመንፈስ ቅዱስ ወንጌል ደም ይንጠባጠባል።

191 እንግዲህ፡ ከጴንጤቆስጤ ዘመን፡ እና ከበዓለ ሃምሳ ሰማዕታት ጀምሮ፡ እስከ ኤፌሶን ቤተ ክርስትያን ድረስ፡ እስከ ጴርጋሞን ድረስ፡ እስከ ትያጥሮን ድረስ፡ ከዚያም አልፎ—እስከ ሰርዴስ፡ በኤፌሶን... ወይም እስከ ፊላደልፊያ፡ ሎዶቅያ ድረስ ይደርሳል። እኛም አሁን... እዚህ የተከሰተው ነገር? ምመጽሐፍ ቅዱስ እንደሚል፡ ነገር ሁሉ ደርሷል፡ አውሬው በዩናይትድ ስቴትስ ይነሣል።

192 በ1933፡ እዚህ የተነበበው ራዕይ ትዝ ይላችኋል? ማለት ይህ ቤተ ክርስቲያንም ገና አልተገነባም ነበር... እና እኔ ገና። ያኔ ራዕይ ምን እንደሆነ አላወቅም ነበር፡ “ምናብ” ብዬ እጠራው ነበር፣ ገና ወጣት የባፕቲስት ሰባኪ ነበርኩ፡ እና ያኔ...

193 ህይወቴ በሙሉ እነዚያን ራእዮች እይቻለሁ፡ የወደቀ ያልተፈጸመ አንድ አለ የሚለኝ ካለ እንዲናገር እጠይቃለሁ። አይ፡ በጭራሽ! ሊሆን አይችልም! እያችሁ? አይሆንም!

194 እና አሁን፡ የስንበት ትምህርት በጀመርኩ ጊዜ በምናብ ተወሰድኩ። ጥቂት ሰዎች ሆነን፡ እዚ በሜሶናውያን ቤት፡ በቻርሊ ከርን ቦታ እንሰበሰብ ነበርን። እና ፕሬዝዳንት ሩዝቬልት ምድርን ወደ አለም ጦርነት ሲመራት እየሁ። ግምት! እንዲህ አልኩ፡ “ከዚያ በመቀጠል ሶስት ርዕዮተ ዓለሞች ይነሣሉ፡ የናዚ፡ እና የፋሺዝም፡ እና ኮሙኒዝም።” ተናግሬአለሁ... (ሰንቶች ታስታውሱታላችሁ? ) “አይናችሁን ኮሙኒዝም ላይ አድርጉ፡ ከሁሉም ከፍ ከፍ ይላል፡” ብዬ ተናግሬ ነበር። “ስለ ኢትዮጵያም፡ ሙሶሎኒ ወደ ኢትዮጵያ ይሄዳል፡ ግን አይሳካለትም፡” ብያለሁ። ሌላም የተናገርኩት፡ “ከጀርመን ጋር ጦርነት መዋጋታችን አይቀሬ ነው፡ ግን” “ጀርመን በከባድ እና በትልቅ ኮንክሪት ውስጥ፡ ትመሸጋለች” አልኩኝ። ይህም የማጅኖት መንገድ ከመገንባቱ ከአስራ አንድ አመት፡ አስራ አንድ አመት በፊት ነው።

195 እንዲህ አልኩ፡ “ከጦርነቱ በኋላ... በመጨረሻው እኛ እናሸንፋለን። እናም ጦርነቱ ካለቀ በኋላ፡ ሳይንስ ታላላቅ ነገሮችን እየፈለሰፈ ይሄዳል።” “እንዲህ በሆኑ ግዜ፡ የሚሰሯት የቤት መኪና አለች፡ እና የቤት መኪኖች ቅርጻቸው ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተቀየረ ይሄዳል።” አልኩኝ። (በ33 ምን ይመስሉ እንደነበር ታውቃላችሁ።) እንግዲህ አሁን፡ አልኩኝ፡ “እንደ እንቁላል ይሆናሉ፡ እንቁላል ይመስላሉ። ምክንያቱ ታላቅ ጎዳና አይቻለሁ፡ እጅግ የተለየ የጎዳናዎች አውራ፡ በዚያም መሪ የሌላቸው መኪኖች ሲሄዱበት አይቻለሁ። የሚቆጣጠራቸው ስልጣን ነበረ።” አሁን ደርሰውበታል።

196 አልኩኝም፡ “በዚያን ጊዜ... አሁን ሴቶች እንዲመርጡ፡ በምርጫ ላይ እንዲሳተፉ፡ ፈቅደውላቸዋል፡ መጨረሻው... ” እንዲህ አልኩ፡ “ይህች አገር በሴታዊ ምልክት የምትታወቅ፡ የሴት አገር ናት። በትንቢት ስለ ሴቶች መብት ተነግሯል፡ በሁሉም ቦታ፡ ትንቢታዊ ቁጥር አሰራ ሶስት በሁሉም ይገኛል።” “አገሩ የሴቶች አገር ነው፡ እዚህ ነጻነት አላቸው። እሷም ታጠፋለች፡ የዓለም መጥፊያ ምክንያት ናት፡” ብዬ ተናግሬአለሁ።

197 (እና፡ ሮይ፡ ደብዳቤዎችህን በዚያ ላይ ደርሰውኛል፡ ያቺ ታላቅ ሴት... “እያንዳንዱ የወንጀል ጉዳይ... መርምረን... አሁንም ኤክስ-ሬ ባደርገው፡ በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ የተፈጸመ እያንዳንዱ የወንጀል ጉዳይ፡ ከበስተጀርባው ሴት አለችበት።” ይህ በትክክል እውነት ነው። አያችሁ፡ ስነምግባር የጎደላቸው ሴቶች፡ ወዘተረፈ።)

198 ያን ጊዜ፡ እንዲህ አልኩ፡ “በዚያ ጊዜ እንዲህ ይሆናል፡ በዚያን ጊዜ ሴቶቹ እንዲመርጡ ይፈቀድላቸዋል፡ በዚህም ምክንያት የተሳሳተ ሰው ይመርጣሉ።” ባለፈው ምርጫ ላይ ይህን አደረጉ። ትክክል ነው። “የምሽጉ ጅማሬ ይህ ይሆናል። በዚያ ጊዜ እንዲህ ይሆናል—በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ ታላቅ ሴት ትነሣለች፡ ቆንጆ አለባበስ የምትለብስ ትሆናለች፡” እና በቅንፍ ውስጥ እላለሁ፡ “(ምናልባት የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን)።” አያችሁ? “ያ በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ ያሉትን ሌሎችን ያሸንፋል፡ በስልጣኑ ላይ የበላይነትን ይይዛል። ስትታይ ቆንጆ ትሆናለች፡ ይሁን እንጂ የመጨረሻ ጨካኝ-ልብ ይኖራታል።”

199 እንዲህም አልኩ; “ከዚያ በኋላ አየሁ፡ እነሆም ዩናይትድ ስቴትስ እብቅ ስትሆን አየኋት። ምንም የቀረ ነገር አልነበራትም።”

200 ያኔ ግምቴ ነበረ። “አሁን ግን፡ **የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል ነው**።”

201 አስቡት! ከእነዚህ ከሰባቱ ግምቶች፡ አሁን አምስቱ ተፈጽመዋል።

202 የካቶሊክ ቤተክርስቲያን፡ ቤተ ክርስቲያንን ጨብጣ ትይዛለች። ያኔ የዘመን ፍጻሜ ይሆናል።

203 እንዲህም ተናገርኩ፡ “እነሆ እያለሁ፡ ጉቶዎች ይነዳሉ፡ አለቶች፡ ይሰነጣጠቃሉ፡ መላው ዩናይትድ ስቴትስ መሬት ላይ ወድቃ፡ ባዶ ትመስል ነበር፡ እኔ በቆምኩበት ሆኜ ያየሁት ርቀት ሁሉ እንዲሁ ነበር።”

204 እናም እንዲህ አልኩኝ፡ “እንደ ጊዜው አካሄድ፡ ይህ የሚሆነው ከ33 እስከ 77 ድረስ ሊፈጸም ይችላል ብዬ፡ ግምቴን አስቀምጫለሁ።” ያን ጊዜ ለማለፍ እጅግ ከባድ መጣበብ ይሆናል።

205 ወዳጆች ሆይ፡ በባሩድ በርሜል ራስ ላይ ተቀምጠናል። ሁሉም ተዘጋጅቷል።

206 አቤት፡ የተስፋው ቃል የሰጠን፡ ቃል የገባልን የሰማይ አባታችን ግን! የክርስቶስ ባርያ መሆን ይደንቃል አይደል? ቃል የገባቸው ነገሮች ሁሉ! አስቧቸው፡ ባለ መብት ነን። አሁን በመካከላችን ነው። እሱ አሁን ከእኛ ጋር ነው፡ የሁሉንም የልብ ሚስጥር ያውቃል፡ ስለእናንተም ሁሉንም ያውቃል፡ እነዚያ ልባችንን አልፈው የሚገቡ እሳቶች፡ ስለ እኛ ያውቃሉ፡ ይወዱናል።

207 ዛሬ ማታ፡ እምነትን ጠብቃ በያዘች፡ በታናሺቱ መንጋ ውስጥ መቆጠራችሁ ደስ አይላችሁምን? ትእዛዙ ያ ነውና "አንተ ታናሽ መንጋ፡ አትፍራ፡ መንግሥቱን ሊሰጣችሁ የአባታችሁ በጎ ፈቃድ ነው። ሰራውን እንዲህ ባያጥር ኖሮ፡ ስጋ የለበሰው ባልዳነም ነበር።" ተመልከቱ፡ የዘመን ፍጻሜ ላይ ደርሰናል።

208 ጴንጤቆስጤዎች ቀዝቅዘዋል፡ ለብ ብለዋል፡ ከእግዚአብሔር አፍ ተተፍተዋል።

209 እዚህ ጋር ጥቂቶች ብቻ ይወጣሉ፡ ጥቂት፡ በመካከላቸው ግን፡ "እነሆ፡ ሙሽራው ይመጣል!" እርሱ ሲመጣ፡ የእነዚህ ጊዜዎች እያንዳንዱ፡ የእነዚህ ጊዜውዎች እያንድንዱ ጊዜ፡ እ... ሰባት ጊዜዎች መኖራቸውን፡ አስታውሱ። እኛ የምንኖርባት ጊዜ አሁን የመጨረሻ**ዋ** ናት። ከእዚህ ጀምሮ ያሉ ደናግል ሁሉ **እዚህ ጋር** ይነሳሉ። አሜን! ኦህ፡ ይህ ምድነው? መንፈስ ቅዱስ ራሱ።

210 ከዚያም ቤተ ክርስቲያን ስትወስድ... እሁድ ምሽት እንደተማርነው፡ ዮሴፍ ራሱን ለገዛ ወንድሞቹ፡ ለእስራኤል ያሰተዋውቃቸው ዘንድ፡ ሙሽራይቱን ወደ ውስጥ አስገባት፡ ማለት፡ ወደ ቤተ መንግስት ውስጥ እንድትገባ አድርጓል። ከአይሁድ ጋር ብቻውን ቆሞ፡ "እኔ ወንድማችሁ፡ ዮሴፍ ነኝ፡" አላቸው።

211 የዋይታ ጊዜ እንደሚኖራቸው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተቀምጧል፡ እያንዳንዱ ቤት ለብቻው ያለቅሳል።

212 "እነዚህ ጠባሳዎች ከወዴት አገኘሃቸው፡" ይሉታል?

"እጅህ... " ይሉታል፡

"የእጆችህ? "

"በወዳጆቼ ቤት፡" ይላቸዋል።

213 "የወጉትም ሁሉ ያዩታል።" በዚያም፡ ዮሴፍ ይቆማል።

214 እርሱም፡ "አትፍሩ... " ዮሴፍም አላቸው፡ "እርስ በርስ አትጣሉ፡ እግዚአብሔር ሕይወትን ለማዳን ሲል ይህን አድርጓል።" የምን? የቤተክርስቲያን፡ የእህዛብ ሕይወት፡ "ስለ ስሙ፡ ከአሕዛብ ስለወጣ ሕዝብ።"

215 ኧረ፡ መጨረሻ ላይ ነን፡ ወንድሞቼ። ይኸው ደርሰናል! የጌታ ስም የተባረከ ይሁን! እንደ ጴንጤቆስጤ ወንድሞች እና እህቶች፡ ይህን የድሮ ቆንጆ መዝሙር፡ አብረን እንዘምር። አሁን፡ እናንተ "እኔ፡ኮ፡ ባፕቲስት ነኝ፡" ትሉ ይሆናል። የጴንጤቆስጤ በረከት ካገኛችሁ ግን ጴንጤቆስጤዎች ናችሁ። ኧህ-ሃህ። በጣም ጥሩ። በጣም ጥሩ።

> ልባችን በክርስቲያን ፍቅር
> አንድ የሚያደርግ ማሰሪያ ይባረክ፡
> የዘመዶች አሳብ ህብረት
> ልክ ከላይ እንዳለው ነው።

216 አሁን ወዳጆች ሆይ፡ ስሙ። በመካከላችን በህይወት ጉዞ ውስጥ፡ በምንም አይነት ሁኔታ ያለ ሰው፡ ምናልባት በልቡ ትንሽ መራራነት የተሰማው ካለ፡ (ስማኝ!) አሁን አስወግደው። አስተካክል፡ ምንም ነገር እንዲሆን አትፍቀድ...

[አንዲት እህት በልሳን ተናገረች። በቴፕ ላይ ባዶ ቦታ። አንድ ወንድም ተረጎመ—አርታዒ።] አሜን። [አንድ ወንድም በልሳን ተናግሮ ተረጎመው።] አሜን። አሜን።

217 ጌታ ኢየሱስ ሆይ፡ ስለ እነዚህ መልእክቶች እናመሰግንሃለን። ግጌታ ሆይ እምነታችንን መጠበቃችንን እንጂ መተዋችን አላሳየንምና፡ አነቃቅቶናል። ኦህ፡ እግዚ አብሔር ሆይ፡ ይህ መንፈስ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንዲቀጥል፡ እጸልያለሁ። አባት ሆይ፡ እንድንያያዝ እርዳን። ከአንተ ጋር ጠብቀን። ጌታ ሆይ፡ በምንኖርበት በዚህ በመጨረሻው የመቅረዝ ዘመን፡ በመካከላችን ተመላለስ። ብርሃናችን ሁን። ጌታ ሆይ፡ በዚህ ታላቅ የጨለማ ጊዜ፡ በላያችን አብራ፡ **መቅረዝ** እና **ከዋክብት** "መጨለሙ" የሚያስረዱ መሆናቸውን አውቀናልና። ጌታ ሆይ፡ በእግዚአብሔር ብርሃን የምንመላለስ፡ የብርሃን ልጆች በመሆናችን ደስ ብሎናል። ልጆችህ ነን እንጂ፡ በእነዚህ በምድር አሳቦች የተጠመድን አይደለንም። አቤቱ ስለዚህም እጅግ እናመሰግንሃለን።

218 እነዚህን መልዕክቶች እንደ ቃልህ ማረጋገጫ ስለላክህ እናመሰግናለን። አባት ሆይ፡ ሁሌም በመካከላችን ክብር ይሁንልህ። ከምድር ምሬት ሁሌ ጠብቀን። ህይወታችን በፊትህ በጎ እና ንጹህ የተቀደሰም ይሆን ዘንድ፡ ቀድሰህ ጠብቀን። ጌታ ሆይ፡ የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ለእያንዳንዳችን ይህን ያድርግ። ትክክል ያልሆነ ነገር ሁሉ፡ ከመካከላችን አንሣ። ጌታ ሆይ፡ ከእኛ ዘንድ ውሰደው። እራስን የመመርመር ጊዜ ነውና።

219 እነዚህ ሰብሰባዎች ልባችንን እንድንመረምር የታሰቡ ናቸው። የዓይኖችህ የእሳት ነበልባል፡ "የልብን ከፍ ያለውን ነገር መርምሮ ያውቃልና።" በእውነት፡ አባት ነህ። አቤቱ መልሰልን ተናገረንም... ሰዓቲቱ ደርሳለችና እርሳችንን እንድናዘጋጅ እርዳን።

220 አቤቱ፡ አባት ሆይ፡ ስለዚህ እጅግ እንባርክሃለን። በጸጋህ በእኛ ባለው ኃይል ሁሉ ይህን እንባርክሃለን። አሜን።

221 ኦህ፡ አትወዱትምን? አሁን፡ በመካከላችን እንግዳ ቢኖር፡ ልክ እንደ መጀመሪያው ነው። ኢየሱስ በዚህ ምድር ሳለ፡ አንድ ሰው ስለ ጋብቻ እና ስለ ፍቺ ጉዳይ ወይም ስለ አንድ ነገር ጠየቀው፡ እንዲህ አላቸው፡ "ከመጀመሪያው እንዲህ አልነበረም፡" አላቸው። ወደ መጀመሪያው መመለስ አለበት።

222 ከመጀመሪያው የነበረ የጴንጤቆስጤ ቤተ ክርስቲያን ከሆነ እና እሱም የወይኑ ግንድ ከነበረ፡ እንግዲያውስ ቅርንጫፎች ነን፡ ያ ግንድ ቤተክርስትያን ባፈራ ቁጥር፡ የጴንጤቆስጤ ቤተ ክርስቲያን፡ የጴንጤቆስጤ ቅርንጫፍ ይሆናል፡ ሁሉ ጊዜ (እያችሁ? )፡ ከመጀመሪያ ጀምሮ ተመሳሳይ ነበረ። እንግዲህ፡ ሌሎች ቅርንጫፎች በላዩ ላይ ብታዳቅሉ የየራሳቸውን ፍሬ የሚያፈሩ ይሆናሉ። የብርቱካን ዛፍ ወስዳችሁ—ሎሚ ብታዳቅሉበት፡ የብርቱካን ህይወት ትቶ ሎሚ ያፈራል። ከጎኑም የወይን ፍሬ አዳቅሉበት፡ የሆምጣጤ ዛፍ :ስለሆነ የወይን ፍሬ ያፈራል።

223 ስለዚህ እነዚህ ድርጅቶችም፡ የኃይማኖት ተቋማትም ቢሆኑ፡ በዚያ ውስጥ ተሰግስገው፡ ክርስትያኖች ነን ቢሉ፡ በክርስትና ሕይወት መኖር ይችላሉ። ይህ በትክክል እውነት ነው፡ ፍሬአቸው ግን የኃይማኖት ተቋም ፍሬ ይሆናል። በትክክል። እንዲሁ የተሰገሰጉ ናቸውና። ቅርንጫፉ ራሱ ግን መቼም ቢሆን...

ወይም ያ ወይን የራሱ ቅርንጫፍ ቢያወጣ፡ ከበስተጀርባው... የኃዋርያት ስራ የሚጽፍ ይሆናል። ይህም በትክክል እውነት ነው። በመጀመሪያ የሆነው ነገር ይህ ነውና። የወጣ ቅርንጫፍ በሙሉ፡ ብርቱካን ያፈራል። መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚልም፡ አስራ ሁለት ቅርንጫፎች እንደነበሩት ይመሰክራል።

224 ኦህ፡ በቅርንጫፍ ሥር በመኖሬ በጣም ደስ ብሎኛ፡ እናንተስ? አዎን፡ ወዳጄ። ኦህ፡ ድንቅ ነው።

225 በጣም ጥሩ፡ ነገ ማታ በፊልደልፊያ ጠርዝ-... ማለት ሰርዴስ ላይ መድረሳችን አስታውሱ። የ... ? ... የማሪቲን ሉተር፡ የሉተራን ድርጅት መምጣት እንማራለን... ? ...

**የትያጥሮን ቤተ ክርስቲያን ዘመን** AMH60-1208

(The Thyatirean Church Age)

**የኢየሱስ ክርስቶስ መገለጥ ተከታታይ ትምህርት**

ይህ መልዕክት በወንድም ዊልያም ማርዮን ብራንሃም በኢንግሊዘኛ የተላለፈ መልዕክት በ ታሕሳስ 8፡ 1960፡ ሐሙስ ማታ፡ በዩ.ኤስ.ኤ.፡ በጀፈርሰንቪል ኢንዲያና፡ ከሚገኘው ብራንሃም ተበርናክል፡ ከማግኔቲክ ቴፕ ቅጂ ተወሰዶ ሳይሸራረፍ ወደ ኢንግሊዘኛ ተጽፏል። ይህ የአማርኛው እትም በቮይስ ኦቭ ጋድ ሪከርዲንግስ ተተርጉሞ ተሰራጭቷል።

AMHARIC

©2023 VGR, ALL RIGHTS RESERVED

VOICE OF GOD RECORDINGS

P.O. BOX 950, JEFFERSONVILLE, INDIANA 47131 U.S.A.

www.branham.org

## የቅጂ መብት ማሳሰብያ

ይህ መጽሐፍ የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ይሰፋ ዘንድ፣ በቤት ለግል ጠቀሜታም ሆነ ለሌሎች ሰዎች ያለ ክፍያ ለማበርከት፣ በቤት ማተሚያን መጠቀም ይቻላል። ይህ መጽሐፍ ያለ ቮይስ ኦፍ ጋድ ሪከርዲንግስ በጽሑፍ የተደገፈ ህጋዊ ፈቃድ መሸጥም ሆነ፣ አብዝቶ ማተም፣ በዌብ ሳይት ላይ ማስቀመጥ፣ በማከማቻ ዘዴዎች ላይ ማስቀመጥ፣ ወደ ሌሎች ቋንቋዎች መተርጎምም ሆነ የድጋፍ ማሰባሰቢያ አድርጎ መጠቀም የተከለከለ ነው። ህጋዊ መብቱም ሁሉ የተጠበቀ ነው።

ተጨማሪ መረጃ ወይም ተጨማሪ ግብዓቶች ከፈልጉ፣ እባኮትን ይህ አድራሻ ይጠቀሙ፡

Voice Of God Recordings
P.O. Box 950, Jeffersonville, Indiana 47131 U.S.A.
www.branham.org